# አንድ አምላክ
# አንድ መንገድ

ለአስተማሪዎች ፤
ለተማሪዎችና ፡
ለሌሎች ፡
የሚረዳ ፡ መጽሐፍ ።

የቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ ድርጅት
ፖ. ሣ. ቁ. 127
አዲስ አበባ ።

# ማውጫ

## የመጽሐፉ ቅደም ተከተል ትምህርቶች ሰሌዳ


ትምህርት — ገጽ

መግቢያ

1. አንድ አምላክ — 3
2. አዳምና ሔዋን — 6
3. ቃየንና አቤል — 8
4. ነቢዩ ኖኅ — 11
5. ነቢዩ አብርሃም — 13
6. ነቢዩ ሙሴ — 16
7. ነቢዩ ዳዊት — 19
8. ኢየሱስ ክርስቶስ — 21
9. ኃጢአት — 25
10. ጸሎትና መልካም ሥራ — 27
11. ወደ ፊት ሊሆኑ ያላቸው ነገሮች — 30
12. አንድ መንገድ — 33

# መምሪያ

1. የመጀመሪያውን ትምህርት አንዴ በፍጥነት አንብበህ ከወጣኸው በኋላ እያንዳን ዱን አንቀጽ በድጋሜ በማንበብ ገብቶህ እንደሆን አረጋግጥ ።
2. ትምህርቱ እንደገባህ ባረጋገጥህ ጊዜ የመልመጃውን ጥያቄ በደንብ አንብበህ ስት ረዳው መልሱን መልስ ። ከዚያም በኋላ ሁለተኛውን ትምህርት እንዲዚሁ ሥራ ። በዚህ ዓይነት ሁሉንም ትምህርት በጥንቃቄ ለመሥራት ሞክር ። በሙሉ ስትጨርስ አርሞ እንዲመልስልህ ለአስተማሪህ መጽሐፉን ስጠው ።
3. ምናልባት ጥያቄ ቢኖርህ ደብዳቤ ጻፍልን ።
4. በዚህ ኮርስ ተደስተህ እንደሁ ለጓደኞችህ ንገራቸውና የዚሁኑ ኮርስ ግልበጭ እንዲያገኙ ይጻፉልን ።
5. በመልመጃው ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ከመለስክ በኋላ አስተማሪህ አርሞ እንዲመ ልስልህ አድርግ ።

# ትምህርት ፩

## አንድ አምላክ ።

«አንድ አምላክ አለ ፤» አንድ አምላክም ብቻ በመኖሩ የተቀሩት አምላኮች መኖር ውሸት ነው ።

ማንኛውም አምላክ የለም የሚል ሰው ስንፍናውን ያስረዳል ። ሰው እግዚአብ ሔርን ለማወቅ ይፈልጋል ፤ ሆኖም የእግዚአብሔርን መኖር ለማወቅ ወደሚኖርበት ዓለም ይመለከታል ። ዓለም እራሱ ፈጣሪ እንዳለው ማወቅ ይፈልጋል ። ልዩ ልዩ ዓይነት ቅርጽ ያላቸው ዛፎችና ሕያዋን እንስሳት እያንዳንዳቸው በትክክል በመሠራት ዘለዓለማዊ የሆነ ደንጋጊ እንዳላቸው ያረጋግጣሉ ። ፀሐይና ጨረቃ እንዲሁም ከዋክ ብት ሠሪ እንዳዘጋጃቸው ይገልጻሉ ፣ እርሱም እግዚአብሔር ነው ። «እግዚአብሔርም በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ።»

በመጀመሪያ ቀን እግዚአብሔር «ብርሃን ይሁን አለ ።» ከመቅጽበት የመጀመሪ ያው ብርሃን በጨለማ ውስጥ ታየ ። እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ ። «እንዲሁም እግዚአብሔር ብርሃኑን ከጨለማ ለየ ፤ እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ፣ ጨለማውን ደግሞ ሌሊት አለው ።»

በሁለተኛውም ቀን ውኃዎችን ለየና ሰማያት እንዲገለጡ አደረገ ።

በሦስተኛውም ቀን እግዚአብሔር ፣ «ከጠፈር በታች ያሉት ውኃዎች በአንድ ሥፍራ ይከማቹና ደረቁ መሬት ይገለጽ አለ ፤ እንዳለውም ሆነ ። እግዚአብሔርም ደረቁን የብስ ምድር ብሎ ጠራው ። የተከማቸውንም ውኃ ባሕር አለው ። እግዚአ ብሔርም መልካም እንደሆነ አየ ።» በዚሁ ቀን ታላቁ አምላክ ምድር ሣርንና ዛፍን እንድታበቅል አደረጋት ። እግዚአብሔርም በፈጠረው ተደሰተ ።

በአራተኛውም ቀን እግዚአብሔር ፀሐይን ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጠረ ። ታላቁ ብርሃን (ፀሐይ) በቀን ላይ ሰለጠነ ። አነስተኛውም ብርሃን (ጨረቃ) በሌሊት ላይ ሰለጠነ ። አዕላፋት ከዋክብት ሁሉ እውነተኛና ነዋሪ በሆነው አምላክ ወደ መሆን መጡ ።

በአምስተኛውም ቀን እግዚአብሔር ዓሣዎች በባሕር እንዲዋኙና አዕዋፋት በሰ ማይ እንዲበሩ ፈጠረ ። እግዚአብሔርም ታላላቅ አንበሪዎችን ውኃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ እንደወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ማለት እንደ ቀኖስና ንስር አሞራ ያሉትን ፈጠረ ።

በስድስተኛውም ቀን እግዚአብሔር እንስሳትንና የምድር ተንቀሳቃሾችን ሁሉ ፈጠረ ። ድቦች ፣ አንበሶች ፣ ዝሆኖች ፣ ጉንዳኖችና ዝንቦች ሁሉ በአንዱ በእውነተኛ አምላክ ወደ መሆን መጡ ። በሥራውም መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር የምድርን ትቢያ አንስቶ ሰውን ለመሥራት «ኑ ሰውን እንፍጠር» አለ ። በአፍንጫውም እስት ንፋስ እፍ አለበት ፣ ሰውም ሕይወት ያለው ሆነ ።

እውነተኛ አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ይህ የምናየውን ትልቅና ውብ የሆነውን ዓለም መፍጠር ይችላል ። አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ አለ ። እውነተኛው አምላክ የዓለማት ሁሉ ፈጣሪ ነው ። እውነተኛው አምላክ ምን ይወዳል ?

ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ከሚረዱን መንገዶች አንዱ እንደሚከተለው ጠባዩን ማጥናት ነው ። ከነዚህም አንዳንዶቹ ፦

1. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በማንኛውም ቦታ ይገኛል ።
   እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በማንኛውም ሥፍራ ከመገኘቱ በላይ ማንም ደግሞ ከእርሱ መሸሸግ አለመቻሉንም ይገልጻል ። ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ሲል ተናገረ ፦ «ከአንተ ወዴት እሸሻለሁ ? ከባሕር ማዶ ብሸገር አንተ ከዚያ ነህ ። በጨለማም ልሸሸግ ብሞክር አንተ ታየኛለህ» ብሎአል ።

2. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል ።
   እግዚአብሔር የልብን ሐሳብና የተሰወረውን የልቦናችንን ሚስጢር ያውቃል ። ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ሲል ተናገረ ፦ «አንተ ሐሳቤ ይገበሃል ፤ በመላሴም ቃል የለም ፤ ነገር ግን አቤቱ ጌታ ሆይ ፤ አንተ ሐሳቤን ሁሉ አጠቃለህ ታውቃለህ ።» ከሰዎች አንዳንድ ነገር መሸሸግ እንችል ይሆናል ፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ምንም መሰወር አንችልም ። «እኔ እንዳላየው እራሱን ሸሽጎ መሰወር የሚችል አለን ? ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ። ሰማይንና ምድርን የሞላሁ እኔ አይደለሁምን ?»

3. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ይቆጣጠራል ።
   እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረ ብቻ ሳይሆን ሥራቸውንም እንዲያከሄዱ የሚያደርግ እርሱው ነው ። የፀሐይን ብርሃንና ዝናብን ይቆጣጠራል ።

4. እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው ።
   መጀመሪያ እንዳልነበረው ሁሉ እንዲሁም ፈጽሞ ፍጻሜ አይኖረውም ። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያለና ወደፊትም የሚኖር ነው ። «ተራራዎች ሳይመሰረቱ ምድርና ዓለማትን ገና ሳትሠራ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አንተ አምላክ ነህ ።»

5. እግዚአብሔር ፍጹም ነው ።
   ማንኛውም የሚያደርገው ነገር ሁሉ ትክክልና እምነት የሚጣልበት ነው ። «ሥራዎችህ ታላቅና አስደናቂ ናቸው ። ጌታ ኃያል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ፤ መንገዶችህ ፍጹምና ቅዱስ ትክክልም ናቸው ።»

6. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ።
   «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅዱስና እጅግም ቅዱስ የሆነ ቅዱስ ነው ።» እግዚአብሔር ወትሮ ቅዱስ እንደነበረ ወደፊትም ፍጹም ቅዱስ ሆኖ ይኖራል ። ይህ ከባሕሪዎቹ አንዱ ነው ። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ኃጢአትን መቅጣት አለበት ። የምናደርገው ክፉ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው ። እግዚአብሔር የምንሠራውን ክፉ ነገር ሁሉ ይጠላል ።

7. እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነው ።

ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ሲል ተናገረ ፦ «ጌታ ሆይ ፣ አንተ መልካምና ይቅር ለማለትም የተዘጋጀህ ነህ ። ስምህንም ለሚጠሩ ሁሉ ይቅርታህ የበዛ ነው» አለ ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር የምናደርገውን ክፉ ነገር ቢጠላ ሊረዳንና ይቅር ሊለን ዝግጁ ነው ። ይወደናል ሆኖም ኃጢአታችንን አይወድም ። እውነተኞችና ፍጹማን እንድንሆን ይወዳል ። ከሁሉ በላይ ግን እግዚአብሔር ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እንዲሁም ልጆች እንዲወዱት ይፈልጋል ።

እግዚአብሔርን ትወዳለህን ? እሱ ይወድሃል ፣ ዳሩ ግን ኃጢአትህን አይወድም ።

## ፩ኛ መልመጃ

### እንድ አምላክ ።

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ ። ትክክሉ ከሦስቱ አንዱ ነው ።

1. እግዚአብሔር የሚገኘው ——
   - ሀ· በአንድ ጊዜ በአንድ ሥፍራ
   - ለ· በአንድ ጊዜ በሁለት ሥፍራ
   - ሐ· በአንድ ጊዜ በሁሉ ሥፍራ ______________

2. እግዚአብሔር በአራተኛው ቀን የፈጠረው ——
   - ሀ· ፀሐይን ጨረቃንና ከዋክብትን
   - ለ· ዓሣንና አዕዋፍን
   - ሐ· ሰውን ______________

3. እግዚአብሔር የሚፈልገው ——
   - ሀ· ወንዶች ብቻ እንዲወዱት
   - ለ· ሴቶች ብቻ እንዲወዱት
   - ሐ· ወንዶች ሴቶችና ልጆችም እንዲወዱት ______________

4. እግዚአብሔር መፍጠር በጨረሰበት ቀን ——
   - ሀ· የብስንና ባሕርን ለየ
   - ለ· ሰውን ፈጠረ
   - ሐ· ብርሃን ይሁን አለ ______________

5. እግዚአብሔር የሚወደው ——
   - ሀ· ኃጢአታችንን
   - ለ· እኛንና ኃጢአታችንን
   - ሐ· እኛን ብቻ ______________

ከትምህርቱ በምታገኘው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑ ምንን ይቀጣል ? ________________

7. እግዚአብሔር በመጀመሪያ ምንን ፈጠረ ? ________________

8. የነበረውና ሁል ጊዜም የሚኖረው ማን ነው ? ________________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. አንድ እውነተኛ አምላክ አለ ። ________________

10. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል ። ________________

# ትምህርት ፪

## አዳምና ሔዋን ።

በመጀመሪያ በምድር ላይ የነበሩት ሁለት ሰዎች አልተወለዱም ነበር ። ከአዳምና ከሔዋን በስተቀር በምድር የኖሩ ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ በሕፃንነት ተወልደው ወደዚህ ዓለም የመጡ ናቸው ። በዚህ በኩል አዳምና ሔዋን ለየት ያለ ልምምድ አላቸው ። እነርሱ በቀጥታ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ፍጡሮች ነበሩ ።

በስድስተኛው ቀን እግዚአብሔር የምድርን ትቢያ አንስቶ ሰውን አበጀ ፤ በአፍንጫውም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ፤ ሰውዬውም ሕይወት ያለበት ነዋሪ የሆነ ሰብዓዊ ፍጡር ሆነ ። ስሙንም አዳም ብሎ ጠራው ። አዳምም በእግዚአብሔር ቀጥተኛ ሥራ ተፈጠረ ።

እግዚአብሔር ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም እንዳልሆነ ስለአስተዋለ እረዳት ሊፈጥርለት አቀደ ። እግዚአብሔርም በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ እንዲመጣበት አደረገ ። አዳምም በአንቀላፋ ጊዜ እግዚአብሔር ከጎኑ አንድ ጎድን አውጥቶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው ። ጎድኑንም ሴት አድርጎ ሠራው ። አዳምም ሴቲቱን ሔዋን ብሎ ጠራት ።

እግዚአብሔርም አትክልትን ተክሎ አዳምንና ሔዋንን በዚያ አኖራቸው ። እንዲህም ሲል መረቃቸው ፤ «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው» አለ ። እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ወደ አዳም አመጣቸው ። «አዳምም ለእንስሳቱ ሁሉ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው ።»

አዳምና ሔዋን ይኖሩበት በነበረው በኤደን ገነት ብዙ ልዩ ልዩ መልካከም ዛፎች ነበሩ ። እግዚአብሔርም አዳምና ሔዋንን እንዲህ ሲል አዘዛቸው ፤ «ከገነት ዛፍ ሁሉ ብሉ ነገር ግን ክፉና ደጉን ከምታስታውቀው ዛፍ እንዳትበሉ» አላቸው ። አዳምና ሔዋን በአትክልቱ ሥፍራ እንዲኖሩ ከተነገራቸው በኋላ ከዛፉ ፍሬ ሁሉ የተቻላቸውን ያህል እንዲበሉ ተፈቀደላቸው ። ነገር ግን ከዚህች ክፉና ደጉን ከምታስታውቀው የዛፍ ፍሬ ከበሉ አጥፊዎች ወይም ሕገ ወጦች እንደሚሆኑ ተነገራቸው ።

ሰይጣንም የእርክሰት የበደልና የሐሰት ሁሉ አባት ስለ ሆነ አዳምንና ሔዋንን በሹክሹክታ ምክሬን ብትሰሙና ከዚህች ከፉና ደጉን ከምታስታውቀው የዛፍ ፍሬ ብት በሉ ዓይኖቻችሁ ይከፈታሉ አላቸው ። «ሴቲቱም ዛፉ ለመብል ያማረ እንደሆነ ለዓ ይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ ።» ሰይጣንም በማታ ለል ሸነገላቸው ።

አዳምና ሔዋንም ከዛፉ ፍሬ በበሉ ጊዜ መራቆታቸውን ስለአወቁ ከአትክ ልቱ ቅጠሎች ሰውነታቸውን ሊሸፍኑ ይሰፉ ጀመር ። ገና ከዛፉ ፍሬ እንደ ወሰዱ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ጀመሩ ። ይህ አድራጎታቸው ኃጢአት ነው ። ይህንን ቀጥተኛ ለእግዚአብሔር ያለመታዘዝ እርምጃ በመውሰዳቸው ኃጢአተኞች ሆኑ ።

እግዚአብሔርም ተጣርቶ ፣ «ይህ ያደረጋችሁት ምንድር ነው ?» አላቸው ። ሴቲቱም ፣ «ሰይጣን አስቶኝ በላሁ አለች ።» እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ሰይጣንን ረገመው ፤«በአንተና በሴቲቱ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ ፣ በዘርዋና በዘርህም መካከል ጠላትነትን አኖራለሁ ። እርሱም እራስህን ይቀጠቅጥሃል አንተም ሰኰና ውን ትቀጠቅጣለህ ።»

እግዚአብሔርም ከቆዳ የተሠራ ልብስ አምጥቶ የአዳምንና የሔዋንን እራቁትነት ሸፈነ ። እንስሳም ታርዶ ቆዳው ለመጎናጸፊያ ተሰጣቸው ። አዳምና ሔዋን በበደሉት በደል ፣ በደል የሌለበት እንስሳ ታርዶ ልብስ ሆነላቸው ።

እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው ከአትክልቱ ሥፍራ አስወጥቶ ሰደዳቸው ። ከዚያም አዳም ምግብ ለማግኘት ምድርን በትጋት ማረስ ግድ ሆነበት ።

በአንድ ሰው አለመታዘዝ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ሆኑ ። «ስለዚህ ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ ፣ ሞትም በኃጢአት ። ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ስለሆኑ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ ደረሰ ።» እኛ ሁላችን የአዳም ልጆች ነን ። ነገር ግን እንደ አዳም ሁላችን ለእግዚአብሔር አልታዘዝንም ። ሁላችንም መልካምን ነገር ከማድረግ ወድቀናል ። ሁላችንም እንደ አዳም በደለኞች ስለሆን መሸፈኛ ያስፈልገ ናል ። አዳምና ሔዋን በቁርበቱ እንዲሸፈኑ እንስሳ ታርዶአል ። እኛም ለኃጢአታ ችን መሸፈኛ የሚሆን ልብስ መፈለግ አለብን ።

## ፪ኛ መልመጃ

### አዳምና ሔዋን ።

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ ። ትክክሉ ከሦስቱ አንዱ ነው ።

1. አዳምና ሔዋን ይበሉት ዘንድ የተፈቀደላቸው የዛፍ ፍሬ ——
   - ሀ. ከፉና ደጉን ከምታስታውቀው የዛፍ ፍሬ በስተቀር ከቀሩት ሁሉ እንዲበሉ
   - ለ. ከፉና ደጉን ከምታስታውቀው ዛፍ ብቻ እንዲበሉ
   - ሐ. በአትክልቱ ከሚገኙት የዛፍ ፍሬዎች ሁሉ እንዲበሉ ____________

2. እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረው —
   ሀ. ከእንጨት ነው
   ለ. ከንድን ነው
   ሐ. ከመሬት ትቢያ ነው ____________

3. አዳም ስምን ያወጣው —
   ሀ. ለከዋክብት
   ለ. ለእንስሳትና ለአዕዋፍ ለአራዊትም ነው
   ሐ. ለእንስሳቶች ብቻ ____________

4. እግዚአብሔር ሔዋንን የሠራት —
   ሀ. ከእንጨት
   ለ. ከጎድን
   ሐ. ከምድር ትቢያ ____________

5. አዳምንና ሔዋንን ከአትክልቱ ሥፍራ ያስወጣቸው —
   ሀ. እግዚአብሔር ነው
   ለ. መላእክ ነው
   ሐ. ሰይጣን ነው ____________

ከትምህርቱ በምታገኛቸው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. ስንት ሰዎች ናቸው ኃጢአትን የሠሩት ? ____________

7. የክፋት የእርክሰትና የውሸት ሁሉ አባት ማን ነው ? ____________

8. ለአዳምና ለሔዋን ሃፍረተ ሥጋ መሸፈኛ እንዲሆን ምን ታረደ ? ____________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ባደረጉ ጊዜ እግዚአብሔርን ያልታዘዙ ሆኑ ። ______

10. ሁላችንም እግዚአብሔርን አልታዘዝንም ። ____________

# ትምህርት ፫

## ቃየንና አቤል ።

ወደዚህ ዓለም በመወለድ በመጀመሪያ ጊዜ የመጣው ወንድ ልጅ ቃየን ነው ። ልጁንም አዳምና ሔዋን ቃየን ብለው ስም አወጡለት ። ለነዚሁ ቤተሰቦች በድጋሚ ሁለተኛ ልጅ ተወለደላቸው ፣ ሁለተኛውም ልጅ አቤል ተብሎ ተጠራ ።

ሁለቱም ወንድማማቾች እንደ አደጉ በተለያየ የሥራ መስክ ላይ ተሠማሩ ። አቤል ያባቱን በጎች ማገድ ይወድ ስለነበረ ጥሩ በሆነ መስክና በመልካም የእረፍት ውኃ ዘንድ ያሰማራቸው ነበር ። አንዳንድም ተናጣቂ የዱር አውሬዎች እንዳይገድ

ሉዋቸው ለመከላከል ይሞክር ነበር። ቃየን ግን ስለ እንስሳት ግድ አልነበረውም። ሆኖም ምድርን መቆፈርና ዛፎችን መትከል ፍሬዎችንና አትክልቶችንም ሲበቅሉ ማየት ደስ ያሰኘው ነበር።

ምንም እንኳ ሁለቱም የተለያየ ሥራ ቢኖራቸው አንዱን እውነተኛ አምላክ ብቻ በማምለክ ይኖሩ ነበር። ስለዚህ የግሉ አድርጎ እንዲጠብቃቸው ስለሚፈልጉ መስዋዕትን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ አቀዱ። ሆኖም የተለያየ መስዋዕት መረጡ። ቃየንም ወደ ዱር ሄዶ ጥቂት ፍሬዎችን ከሜዳ ለቅሞ ለእግዚአብሔር መስዋዕትን አቀረበ። በአንድ ዓይነት አስተሳሰብ ብንመለከት ቃየን ያቀረበው መስዋዕት የእጆቹን ሥራ የሚያመለክት ነው። መሬቱን ቆፈረ ዘሩንም ዘራ ፍሬውም በበሰለ ጊዜ ለቀመ። በሌላ ዓይነት አነጋገር ቃየን ይህን ሲያደርግ፣ እግዚአብሔርን «ተመልከት! ይህ በጥረቴ ያስገኘሁት እጄ የሠራው ነው ብሎ ማመልከቱ ነው።»

የአቤል መስዋዕት ግን ፍጹም የተለየ ነበረ። ከመንጋው የሰባውን መርጦ ለእውነተኛው አምላክ መስዋዕት አቀረበ። እግዚአብሔርም በአቤል መስዋዕት ተደስቶ ተቀበለው። የቃየንን መስዋዕት ግን አልተቀበለም፣ ምክንያቱም ተፈላጊው ዓይነት መስዋዕት ስለ አልነበረ ነው።

አቤል በእግዚአብሔር ሥራ የሚያምን ሰው ሳለ ቃየን ግን በራሱ ሥራ ይመካ ነበር። እግዚአብሔር የአቤልን በግ ስለተቀበለውና የእርሱን ፍሬ ስለ አልተቀበለው ቃየን ተመቀኘ። በጣምም ተቆጥቶ አቤልን ለመግደል አቀደ። አንድ ቀንም በሜዳ ሲሠሩ ሳለ ቃየን ወንድሙ አቤልን ገደለው። ይህም የመጀመሪያው ግዳይ ነበረ።

ቃየን አቤልን ስለገደለው እግዚአብሔር በቃየን በጣም አዘነበት። ስለዚህም እግዚአብሔር ቃየንን በኃይል ሊቀጣው ተነሳ። እግዚአብሔር ቃየንን ስለሠራው ክፉ አድራጎት ረገመው፤ ቃየንም ወንድሙን በመግደሉ በቀረው ዘመኑ ሁሉ ቅጣትን ተቀበለ።

ቃየንና አቤል አማኞች በመሆናቸው ሁለቱም በእውነተኛው አምላክ ማመናቸውን ይመሰክሩ ነበር። አንድ ሰው አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ በማወቅ እርግጠኛ መሆኑ አይበቃውም፤ እውነተኛውን አምላክ ብቻ ለማምለክ የምናደርገው ጥረት ብቻውን በቂ አይደለም። ይህንንም ስንል እንደ አቤል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን እንድናገኝ ትክክለኛው ዓይነት መስዋዕት ሊኖረን ይገባል ማለታችን ነው። ቃየን ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበው የሚችለውን ትክክለኛ ዓይነት መስዋዕት መምረጥ ይገባው ነበር። ሆኖም በዚህ ፋንታ የራሱን ሞያ የሚያመለክተውን የምድር ፍሬ ለማምጣት አቀደ። በዚህም አድራጎቱ የተሳሳተ ምርጫ መረጠ።

አንተም የግል ምርጫ ሊኖርህ ይገባል። ምን ዓይነትም መስዋዕት ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ማቅረብ እንደሚገባህ መምረጥ አለብህ። ምርጫህንም ከቃየን ምርጫ ጋር በማመሳሰል የእጅህን ሥራ ማቅረብ ትችላለህ። ሆኖም እግዚአብሔር ሊቀበልህ አይችልም፤ አይቀበልህምም። ስለዚህ እግዚአብሔር የተቀበለውን ዓይነት ማለት የአቤልን መስዋዕት የመሰለውን መስዋዕት ለማቅረብ ምረጥ። እግዚአብሔር የሚቀበለው ትክክለኛው ዓይነት መስዋዕት ሊኖርህ ይገባል።

# ፫ኛ መልመጃ

## ቃየንና አቤል ።

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ ። ትክክሉ ከሦስቱ አንዱ ነው ።

1. አቤል ——
   ሀ. በገዛ ሥራው ይታመን ነበር
   ለ. በቃየን ይታመን ነበር
   ሐ. በእግዚአብሔር ይታመን ነበር ______________

2. አቤል መሆን ይፈልግ የነበረው ——
   ሀ. እስፖርተኛ
   ለ. ገበሬ
   ሐ. እረኛ ______________

3. እግዚአብሔር አቤልን የተቀበለበት ምክንያት ——
   ሀ. አንድ አምላክ መኖሩን ስለሚያምን ነው
   ለ. መልከም ልጅ ስለ ነበረ ነው
   ሐ. ትክክለኛውን ዓይነት መስዋዕት ስለአቀረበ ነው ______________

4. ቃየን መሆን ይፈልግ የነበረው ——
   ሀ. እስፖርተኛ
   ለ. ገበሬ
   ሐ. እረኛ ______________

5. የመጀመሪያውን ግዳይ የፈጸመው ——
   ሀ. ቃየን
   ለ. አቤል
   ሐ. አዳም ______________

ከትምህርቱ በምታገኛቸው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. ቃየን በምን ተመካ ? ______________
7. አቤል መስዋዕት አድርጎ ያቀረበው ምንድር ነው ? ______________
8. እግዚአብሔር ማንን ነው የረገመው ? ______________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. ሁለቱም ማለት አቤልና ቃየን እግዚአብሔርን አምነዋል ? ______________
10. የቃየንን መስዋዕት የሚመስል መስዋዕት ለእግዚአብሔር ማቅረብ አለብን ?

______________

# ትምህርት ፬

## ነቢዩ ኖኅ ።

### የመጭው ፍርድ ተናጋሪ መልእክተኛ

ከአቤልና ከቃየን በኋላ ኖኅ ሁለት መቶ ዓመት ኖረ ። በነዚህም ዓመታት ውስጥ ብዙ ሺህ ሰዎች ተወለዱ ። በምድርም ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ከእውነተኛው አምላክ ዘወር ብለው በአማልክቶች ማምለክ ጀመሩ ። ኖኅ በተወለደ ጊዜ ዓለም እስከፊ በሆነ ይዞታ ላይ ትገኝ ነበር ። ሕዝቡም ከግምት በላይ በሆነ አስከፊ እርከ ሰት እራሳቸውን ያበከሉ ነበር ። «እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ ታላቅ እንደሆነና የልቡም ሐሳብ አከታትሎ ክፋት የሚያስብ መሆኑን ተመለከተ ። እግዚአ ብሔርም ምድርን አየ ፣ እነሆም ተበላሽታለች ፤ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በምድር ላይ መንገዱን አበላሽቶ ነበርና እግዚአብሔር ኖኅን አለው ፣ የሥጋ ሁሉ ፍጻሜ በፊቴ ደርሶአል ፤ ከእነርሱ የተነሳ ምድር በግፍ ተሞልታለችና እኔም እነሆ ከምድር ጋር አጠፋቸዋለሁ ።»

እግዚአብሔርም ኖኅን (ትልቅ ታንኳ) ማለት መርከብ እንዲሠራ ነገረው ። ይህ ኖኅና ቤተሰቡ ከሚመጣው አሰቃቂ ቁጣ እንዲያመልጡ ከእግዚአብሔር የተለገ ሳቸው ስጦታ ነው ። ኖኅ መርከቡን በሚሠራበት ጊዜ ለሕዝቡ ይሰብክ ነበር ። ስለሚ መጣው የእግዚአብሔር ቁጣ ያስጠነቅቃቸው ነበር ። እግዚአብሔር ቅን መሆኑንና በኃጢአተኝነታቸውም ምክንያት እንደሚደመስሳቸው አስረድቶአቸዋል ። ይቅር ይላቸው እንደሆነ በኃጢአታቸው ተናዘው ወደ እግዚአብሔር ከክፋታቸው መመለስ እንዳለባቸውም ነግሮአቸዋል ።

ሆኖም ሕዝቦቹ ወደ ስብከቱ አላደመጡም ፣ ምክሩንም ልብ አላሉም ። በዚህ ፋንታ ግን ይስቁበትና ያላግጡበት ነበር ። ኖኅም ወደ ሥራው ፍጻሜ የደረሰበት ጊዜ መጣ ። ጌታም ኖኅን አለው ፤ አንተና ቤተሰብህ ወደ መርከቡ ግቡ ፣ በዚህ ትውልድ መሐከል ጻድቅ ሆነህ አግኝቼሃለሁና ።

እግዚአብሔር እንስሳትንና አዕዋፋትን ሁሉ ማጥፋት አልፈለገም ነበር ። ስለዚህ እግዚአብሔር ኖኅ ከራሱ ጋር ከእንስሳት ፣ ከአዕዋፋትም ፣ ከዱር አራዊትም ሁሉ ተባ ዕትና እንስት እያደረገ ወደ መርከቡ እንዲያገባ አዘዘው ። ኖኅም ከሦስቱ ልጆቹና ከልጆቹ ሚስቶች ጋር ወደ መርከቢቱ ከገባ በኋላ እግዚአብሔር በሩን ዘጋ ። በዚ ያን ጊዜም ኖኅ ቤተሰቦቹና እንስሳቱ ሁሉ በመርከቡ ውስጥ ነበሩ ። ለኖኅ መልእክት ያልታዘዙት ግን በውጭ ነበሩ ።

የእግዚአብሔርም የፍርድ ቀን ጀመረ ። ዝናብም ከሰማይ ጎረፈ ። ጎርፍም በም ድር ሁሉ ላይ ነበር ። ሕዝቡም ወደ ተራራውና ወደ ከረብታው ሮጡ ። ነገር ግን ከሰማይ በታች ያሉ ከፍተኛ ከረብታዎችና ተራራዎች ሁሉ በውኃ ተሸፍነው ነበር ። በምድር ላይ የሚኖር ሥጋ ለባሽ ሁሉ ማለት እንስሳውም ፣ በክንፍ የሚበረውም ፣ በልብ የሚሳበውም ፣ በዱር የሚኖር አራዊትና ሰው ሁሉ ሞተ ።

እግዚአብሔር ለምን ይህን በሰው ልጆች ላይ ፈጸመ? በኃጢአታቸው ምክን ያት ነው። እግዚአብሔር ወደ ምድር ከላከው አሰቃቂ ሞት የዳኑት በመርከቡ ውስጥ የገቡት ብቻ ናቸው። ኖኅም ሆነ ቤተሰቦቹ በመርከቡ ውስጥ ተገን አግኝተ ዋል። እነዚያ ኃጢአትን የሠሩና የእግዚአብሔርን ምክር ለመስማት ያልፈቀዱት ግን ጠፉ።

የእግዚአብሔር ፍርድ የሆነው (ዝናብ) በሕዝቡ ላይ ወርዶ ደመሰሳቸው። የእግዚአብሔር ፍርድ የሆነው (ዝናብ) በመርከቢቷ ላይ ወርዶ ነበር፤ ሆኖም በመር ከቧ ውስጥ ያሉት ተርፈዋል። መርከቢቱ የእግዚአብሔርን የፍርዱን መከራ ተቀበ ለች፤ ይሁንና በውስጧ የነበሩት ምንም ዓይነት ፍርድ አልደረሰባቸውም።

እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ኃጢአትን የሚያደርጉትን ሁሉ መቅጣት አለበት። ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን በማድረግ ወንጅለዋል። እንደ ኖኅ መጠጊያ ካልኖረህ በስተቀር ኃጢአትን ስለ አደረግህ የእግዚአብሔርን የፍርዱን መከራ ትቀበላለህ። ከቁጣው እንድታመልጥ እግዚአብሔር መጠጊያ አዘጋጅቶል ሃል። ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ ትፈልጋለህን?

# ፬ኛ መልመጃ

## <u>ነቢዩ ኖኅ።</u>

### የመጭው ፍርድ ተናጋሪ መልእክተኛ

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ። ትክክሉ ከሦስቱ አንዱ ነው።

1. እግዚአብሔር ኖኅ እንዲሠራው የጠየቀው ——
   - ሀ. መርከብ (ትልቅ ታንኳ)
   - ለ. ጉድጓድ
   - ሐ. ቤት ____________
2. አንዱ ብቻ መጠጊያ ሥፍራ ——
   - ሀ. ከተራራ በላይ ነበር
   - ለ. በመርከብ ውስጥ ነበር
   - ሐ. በምድር ላይ ነበር ____________
3. እግዚአብሔር ወደ ሰብዓዊ ፍጡሮቹ ተመልክቶ ያየው ——
   - ሀ. መበላሸታቸውን
   - ለ. መልካምነታቸውን
   - ሐ. ጥሩ ጊዜ እንደነበራቸው ____________
4. መርከቡ የመጠጊያ ሥፍራ የነበረው ——
   - ሀ. ለኖኅ ብቻ
   - ለ. ለእንስሶች ብቻ
   - ሐ. ለኖኅና ለሚስቱ እንዲሁም ለቤተሰቡና ለእንስሳቱ ____________

5. ኖኅ ለሕዝቡ እንደሰበከላቸው ሕዝቡ ——

ሀ. ጥሩ ሰባኪ ነው አሉ

ለ. ያለውን አመኑ

ሐ. በማላገጥ ሳቁበት ______

ከትምህርቱ በምታገኛቸው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ።

6. የእግዚአብሔር ሰዎች ያደሙት በማን ላይ ነው ? ______

7. ስንት ሰዎች ናቸው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ስለአደረጉ ወንጀለኞች የሆኑት ? ______

8. ማን ነበር የመርከቡን በር የዘጋው ? ______

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ ብንፈልግ መጠጊያ ሊኖረን ይገባል። ______

10. እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ሊል ዝግጁ ነው ። ______

# ትምህርት ፮

## ነቢዩ አብርሃም ።

### የእግዚአብሔር ወዳጅ

አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ በነበረው እምነቱ የታወቀ ነበር። አንድ ቀን እግዚአብሔር አብርሃምን ሀገሩንና ወገኖቹን ትቶ ወደ ሌላ ሀገር እንዲሄድ ጠየቀው። አብርሃምም እግዚአብሔርን ታዘዘ። ወዴት እንደሚመራውም ሳያውቅ በእምነት ቤቱን ትቶ ወጣ። እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ «ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፣ እባርክሀማለሁ፣ ስምህንም ታላቅ አደርገዋለሁ፣ አንተም የተባረክህ ትሆናለህ፣ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፣ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፣ በአንተም ዘር የዓለም አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ» አለው።

አብርሃምም ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት፣ ስማቸውም እስማኤልና ይስሐቅ ይባላል። አንድ ቀን አብርሃም ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ ሳለ እንዲህ ሲል እግዚአብሔርን ጠየቀ፣ «አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፣ እስማኤል በፊትህ ይኑር።» የአብርሃም ታላቅ ፍላጎት እስማኤልና የቀሩት ልጆቹ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን እንዲያገኙ ነበር።

እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ «ስለ እስማኤል ሰምቼሃለሁ፣ እነሆ ባርኬዋለሁ፣ ፍሬያማም አደርገዋለሁ፣ እጅግም አበዛዋለሁ፣ አሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፣ ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ።»

እግዚአብሔር የእስማኤል ልጆች ሁሉ በፊቱ ተቀባይነትን አግኝተው እንዲኖሩ ይፈልጋል። እያንዳንዳቸውም በየግል እንዲወዱትና እንዲያገለግሉት ይፈልጋል። ሆኖም ከእስማኤል ልጆች ማናቸውንም ከነኃጢአታቸው መቀበል አይችልም። ከኃጢአታቸው የነጹ መሆን አለባቸው። «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን

ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው።» በዚህ ትምህርት መጀመሪያ አብርሃም ሊታወቅ የቻለው በታላቅ እምነቱ ነው ብለናል። ምናልባትም የአብርሃም ታላቅ እምነት የተፈተነው እግዚአብሔር ልጁን ወስዶ እንዲሰዋለት በጠየቀው ጊዜ ይሆናል።

አንድ ቀንም እግዚአብሔር አብርሃምን፣ «አብርሃም አብርሃም ሲል ጠራው፤ አብርሃምም መልሶ እነሆ እዚህ ነኝ አለ። እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ የምትወደውን ልጅህን ውሰድና ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ እኔም በምነግርህ ተራራ ላይ መስዋዕት አድርገህ ሰዋው» አለው።

አብርሃምም በማለዳ ተነስቶ አህያውን ጫነ፣ ሁለቱንም ሎሌዎቹን ከእርሱ ጋር አስከተለ፣ በሦስተኛውም ቀን አብርሃም ዓይኑን አንሥቶ በታውን ከሩቅ አየ።

አብርሃምም ሎሌዎቹን «አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን ወደ እናንተም እንመለሳለን» አላቸው። አብርሃም'ና ይስሐቅ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ሥፍራ ሲሄዱ ሳለ ይስሐቅ አባቱን እንዲህ ሲል ጠየቀው፣— አባቴ ሆይ፣ ከሚሰዋው እንስሳ በቀር ለመስዋዕት የሚሆኑ ነገሮችን ሁሉ ይዘናል፤ እነሆ የመስዋዕቱ በግ የታለ አለው። አብርሃምም ልጁን ዘወር ብሎ «እግዚአብሔር የሚሰዋውን በግ ያዘጋጃል» አለው።

እግዚአብሔር ወደ ነገረው ሥፍራ በደረሱ ጊዜ አብርሃም እንጨት የተረበረበ በትን መሰዊያ ሠርቶ ልጁን አስሮ በእንጨቱ ላይ አጋደመው። ከዚያም ካራውን ከእርቱ መዞ ልጁን ሊሰዋው ሲቃጣ ከሰማይ የእግዚአብሔር መልአክ «አብርሃም አብርሃም» ሲል ጠራው።

«በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ እንዳችም አታድርግበት እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ አውቄአለሁና» አለው።

አብርሃምም ዓይኑን አነሣ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በሐረግ ተይዘው አየ። አብርሃምም በጉን ወስዶ በልጁ ፋንታ መስዋዕት አድርጎ ሰዋው። በጉ የተሰዋው በምትክነት ነበር። በጉ የአብርሃምን ልጅ ሥፍራ ወሰደ። የበጉ ደም በአብርሃም ልጅ ፋንታ ፈሰሰ። በደል የሌለበት ንጹሁ በግ ያለበደሉ ተሰዋ።

አንተ ኃጢአትን ሰርተሃል እግዚአብሔር ወደ ኃጢአት መመልከት ስለማይሆን ለት ኃጢአትን አይመለከትም። እግዚአብሔር ኃጢአትን መቅጣት አለበት። ኃጢ አትህ ካንተ ላይ ካልተወገደልህ እግዚአብሔር የሚቀበለው ሰው ሆነህ መገኘት አት ችልም። ኃጢአትህንም አንተ ከራስህ ላይ ለማስወገድ አትችልም። ሌላ ሰው ይህን ሊያደርግልህ ይገባል።

ልክ በጉ የአብርሃምን ልጅ ሥፍራ እንደወሰደ እንደዚሁም በአንተ ፋንታ ሆኖ ሥፍራህን የሚወስድልህ ሊኖርህ ይገባል። ያም በአንተ ፋንታ የሚተካው የግል ኃጢአት ሊኖረው አይገባም። የግል ኃጢአት ካለበት የአንተን ኃጢአት ማስወገድ አይችልም። የአንተን ኃጢአት ለማስወገድ እራሱ ኃጢአት የሌለበት ሰው ሊኖርህ ይገባል። እንዲህ ያለ ሰው ብታገኝ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ታገኛለህ።

ይህንን ሊያደርግልህ የሚችለውን ማወቅ ትፈልጋለህን ? በንባብ ጥናትህ ቀጥል በንተ ፋንታ ሊተካ ስለሚችለውና ስለሚተካው ታነበለህ ።

## ፭ኛ መልመጃ

### ነቢዩ አብርሃም ።

### የእግዚአብሔር ወዳጅ

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊልደ ጻፍ ። ትክክሉ ከሦስቱ አንዱ ነው ።

1. በአብርሃም ልጅ ፋንታ ታርዶ የነበረው እንስሳ ——
   - ሀ. ላም ናት
   - ለ. ፈረስ ነው
   - ሐ. በግ ነው ____________
2. እግዚአብሔር የእስማኤልን ልጆች ሊቀበላቸው የሚችለው ——
   - ሀ. ከነኃጢአታቸው ነው
   - ለ. ከኃጢአታቸው በንጹ ጊዜ ነው
   - ሐ. መልካም ሥራቸው ከክፉ ሥራቸው ሲበልጥ ነው ____________
3. አብርሃም ሊታወቅ የቻለው ——
   - ሀ. በኃጢአቱ ነው
   - ለ. በግመሎቹ ነው
   - ሐ. በእግዚአብሔር ላይ ባለው እምነቱ ነው ____________
4. ኃጢአታችን ሊወገድልን የሚችለው ——
   - ሀ. በሰይጣን ነው
   - ለ. የግል ኃጢአት በሌለበት ሰው ነው
   - ሐ. በገዛ እራሳችን ኃይል ነው ____________
5. ወደ ኃጢአት መመለከት የማይችለው ——
   - ሀ. እግዚአብሔር ነው
   - ለ. ሰው ነው
   - ሐ. መልአክ ነው ____________

ከትምህርቱ በምታገኘው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. አብርሃም እስማኤል ምን እንዲደረግለት ጸለየ ? ____________
7. እግዚአብሔር አብርሃምን የሚረግሙትን ምን ሊያደርጋቸው ተስፋ ሰጠ ?

____________

8. የአብርሃም እምነት የተፈተነበት ትልቁ ፈተና ምን ነበር ?

____________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ።

9. እግዚአብሔር አብርሃም ልጁን መስዋዕት አድርጎ እንዲሰዋው ጠየቀው። ____

10. በጉ ምትክ ነበር። ____________________

# ትምህርት ፮

## <u>ነቢዩ ሙሴ።</u>

### የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ

ሙሴ በምድር ይኖሩ ከነበሩት አስደናቂ መሪዎች አንዱ ነው። አርባ ዓመት በፈጀ ጉዞ ከሚሊዮን የሚበልጡ ሕዝቦችን መርቶአል። ባሁኑ ጊዜ ይህን ያህል የሚበዛውን ሕዝብ በበረሃ ውስጥ የሚመራ ሰው ቢኖር ይህ አድራጎቱ ከጅልነት ያስቆጥረዋል። ሆኖም ሙሴ ይህን አዳጋች የሚመስለውን ተግባር ፈጽሞአል። ወደዚህ ታላቅ መሪ ሕይወት እንመልከት።

ሙሴ የተወለደው በግብፅ ነው። ቤተሰቦቹ በታላቁ በግብፃውያን ፈርዖን ሥር በባርነት ይገዙ የነበሩ እስራኤላውያን ናቸው። ይህም ፈርዖን ወንዶች የሆኑ የበሬ ያዎቹ ልጆች በሚወለዱ ጊዜ እንዲገደሉ ጥብቅ የሆነ የፍርድ ትእዛዝ ሰጠ። ሙሴ በተወለደ ጊዜ እናቱ ይሞትብኛል ብላ ስለፈራች በቤትዋ ውስጥ ለሦስት ወር ያህል ሸሸገችው። ለበለጠ ጊዜ መሸሸግ እንደማትችል በተረዳች ጊዜ ቅርጫት ሰርታ በዚያ ውስጥ አኖረችው። ቅርጫቱንም ይዛ ወደ ወንዝ በመውረድ በውኃ ላይ አን ሳፈፈችው። ከጥቂት ጊዜም በኋላ የፈርዖን ሴት ልጁ ወደ ወንዝ ወርዳ ስለነበር ቅርጫቱ በውኃ ላይ ሲንሳፈፍ አየች። ቅርጫቱንም በከፈተች ጊዜ ሕፃኑን ሙሴን አገኘችው። ለልጁም አሳዳጊ አዘጋጅታ ኋላም ወደ አባቷ ቤተ መንግሥት እንዲ መጣ ትእዛዝ ሰጠች።

ሙሴም ባደገ ጊዜ በግብፅ የሚሰጠውን ማንኛውንም ዕውቀት ተማረ። እርሱም በጣም አስተዋይ ሰው ነበር። ሙሴ ምንም በፈርዖን ቤተ መንግሥት ቢኖርም ግብ ፃዊ አለመሆኑን ያውቅ ነበር። አንድ ቀን በመንገድ ላይ ሲጓዝ ሳለ አንድ ግብፃዊ አንድ እስራኤላዊን ባርያ ሲመታ አየ። ሙሴ ይህንን አድራጎት አልወደደም፤ ምክ ንያቱም እርሱ እራሱ እስራኤላዊ ስለ ነበረ ነው። «ሙሴም ወዲያና ወዲህ ተመል ክቶ ማንም አለመኖሩን ካየ በኋላ ግብፃዊውን ገደለው።» ፈርዖንም ይህንን ሰምቶ ሙሴን ለመግደል አሰበ፤ ሆኖም ሙሴ ወደ በረሃ ከብልሎ በዚያ አርባ ዓመት ቆየ።

አንድ ቀንም ሙሴ በጎች ሲያግድ ሳለ ቁጥቋጦ ሲነድ አየ። ይህም እሳት ከቀ ረው እሳት ሁሉ የተለየ ነበር። ምክንያቱም እሳቱ በሚነድበት ጊዜ ቁጥቋጦው አይ ቃጠልም ነበርና ነው። ሙሴ በግልጽ ለመመልከት ቀረብ ባለ ጊዜ ሙሴ ሙሴ እያለ የሚጣራ ድምጽ ሰማ። ሙሴም መልሶ «እነሆኝ አለ።»

እግዚአብሔርም ከቁጥቋጦው ውስጥ እንዲህ ሲል ተናገረው፤ «ወደዚህ አትቅ ረብ የቆምክበት ሥፍራ ቅዱስ ስለሆነ ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው።» እግዚ አብሔርም በግብፅ በባርነት የሚያለቅሱትን ድምጽ መስማቱንና ነፃም እንደሚያወጣ

ቸው ለሙሴ ነገረው ። እግዚአብሔርም ሙሴን «እኔ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ አንተም የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ መርተህ ታወጣቸዋለህ አለው ።»

ሙሴም እግዚአብሔርን ወደ ፈርዖን ዘንድ ሄጄ የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ ? አለው ።

እግዚአብሔርም እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ብሎ መለሰለት ።

ሙሴም እግዚአብሔርን በመታዘዝ ፈርዖንን ሕዝቡን ከባርነት ልቀቅ አለው ። ፈርዖንም እየሳቀ ሙሴን እስራኤላውያን ከግብፅ አይወጡም ብሎ መለሰለት ። ፈርዖን እስራኤላውያንን ለመልቀቅ አሻፈረኝ ስላለ እግዚአብሔር መቅሰፍትን በግብፃውያን ላይ ላከ ። በምድሩ ላይ የነበረ ውኃ ሁሉ ወደ ደም ተለወጠ ። ከዚህም በስተቀር በብዙ ሚሊዮን በሚቆጠሩ ጓጉንቸሮች፣ቅማልና ዝንቦች እንዲሁም አንበጣዎች ምድሪቷን ቀጣት ። ሕዝቦቹም በአበጭ ታመሙ ፤ ሰማዩም ጠቆረ ፤ የበረዶ ድንጋይም ወደ ምድር ዘነበ ። እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ መቅሰፍት በግብፅ ላይ ያመጣው ፈርዖን እስራኤላውያንን እንዲሄዱ ባለመልቀቁ ነው ።

ሙሴም እንደገና ወደ ፈርዖን ዘንድ ሄዶ «አንተ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝህ ሌላ አንድ ተጨማሪ መቅሰፍት በሕዝብህ ላይ ሊያወርድ ነው አለው ። በእኩለ ሌሊትም ከየቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ የሆነ ሁሉ ይሞታል» አለው ።

ሙሴም በግብፅ የሚኖሩ ሁሉ የቤታቸውን መዝጊያ መቃኑንና ጉኑን የበግ ደም እንዲቀቡት ካሳሰባቸው በኋላ ይህንን ትእዛዝ ተቀብለው ቢፈጽሙ እንደሚድኑ ነገራቸው ። የእግዚአብሔርም መልአክ ደም በተቀባው ቤት ሁሉ ላይ አለፈ ። እግዚአብሔርም ደምን በየሁ ጊዜ መቅሰፍቴ ታልፋችኋለች ብሎ ነበርና ደም ባልተቀባው ቤት የሚኖሩ የመጀመሪያዎቹ ልጆች ሁሉ ሞቱ ። በዚያች ሌሊትም በምድረ ግብፅ እጅግ ብዙ ልጆች ሞቱ ። ሆኖም የእስራኤል ልጆች ደምን በመዝጊያቸው ላይ በመቀባታቸው ከእግዚአብሔር ፍርድ አመለጡ ።

አንተ በኃጢአተኛነትህ ከሞት ፍርድ በታች ስለሆንክና የዚህም «የኃጢአት ዋጋ ሞት ስለ ሆነ መሞት» ይገባሃል ። ከዚህም በስተቀር በዚሁ ኃጢአትህ ከእግዚአብሔር ተለይተህ መበረር አለብህ ። የሆነ ሆኖ እግዚአብሔር ቁጣው የዘገየ ምህረቱ የበዛ ስለ ሆነ ከቁጣው ፍርድ ማምለጫ መንገድ አዘጋጅቶልሃል ። እግዚአብሔር «ደሙን በየሁ ጊዜ አልፍሃለሁ ሊልህ እንዲችል እንደ እስራኤላዊያኖቹ ልብህንና ሕይወትህን በደሙ መቀበት ያስፈልግሃል ።»

ደሙን እንዴት መቀበት ትችላለህ ? የምትቀበውስ ምን ዓይነት ደም ነው ? ጥናትህን ቀጥል በቅርቡ መልሱን ታገኛለህ ።

# ፯ኛ መልመጃ

## ነቢዩ ሙሴ ።

### የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ ። ትክክሉ ከሦስቱ አንዱ ነው ።

1. ሙሴ ——
   ሀ. አንድ መቶ ሰዎችን ወደ ግብፅ መራ
   ለ. አሥር ሺህ ሰዎችን ወደ ምድረ በዳ መራ
   ሐ. ከሚሊዮን የሚበልጡትን ሰዎች ከግብፅ መርቶ አወጣ ______________
2. ሙሴ የተወለደው ——
   ሀ. በሊብነን
   ለ. በግብፅ
   ሐ. በፓለስቲና ______________
3. የኃጢአት ዋጋ ——
   ሀ. የዘለዓለም ሞት ነው
   ለ. የዘለዓለም ሕይወት ነው
   ሐ. መንግሥተ ሰማይ ነው ______________
4. እግዚአብሔር ወደ ፈርዖን ——
   ሀ. ኖኅን ላከ
   ለ. አቤልን ላከ
   ሐ. ሙሴን ላከ ______________
5. እግዚአብሔር ምን በየሁ ጊዜ ሕዝቡን አልፋለሁ አለ ——
   ሀ. ደም
   ለ. ውኃ
   ሐ. በግ ______________

ከትምህርቱ በምታገኘው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. ሙሴ ምን ሲቃጠል አየ ? ______________
7. ከፍርድ የማምለጫውን መንገድ ማን አዘጋጀ ? ______________
8. ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥተን ለምን እንሰደዳለን ? ______________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. ሙሴ ግብፃዊውን ገደለ ። ______________
10. እግዚአብሔር በእስራኤላውያን በሮች ላይ መቅሰፍቱን ላከ ። ______________

# ትምህርት ፯

## ነቢዩ ዳዊት ።

### እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ሰው

ነቢዩ ዳዊት ታላቅ ሙዚቀኛ እንደመሆኑ መጠን መዝሙራትን መጻፍና በገና ውን በመደርደር መዝሙሮቹን መዘመር ይወዳል ። አንዳንዶቹም እርሱ የጻፋቸው መዝሙሮች በሕይወቱ የተለማመዳቸውን ነገሮች ይነግሩናል ።

ከዕለታት አንድ ቀን ዳዊት በብሩህ የሌሊት ከዋክብት ብርሃን የአበቱን በጎች ሲያግድ አሻቅቦ ወደ ላይ ተመልክቶ ኖሮ የከዋክብቶቹን ብርሃን በማድነቅ የሚከተለውን መዝሙር ጻፈ ።

አቤቱ ጌታ ጌታችን ሆይ ፥ ስምህ በምድር ሁሉ እንዴት ያማረ ነው ? ከሰማያት በላይ ክብርህን ማን አኖረው ? የጣቶችህን ሥራ ሰማያትን በየሁ ጊዜ ጨረቃና ከዋክብትን ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው ?

ነቢዩ ዳዊት በታላቁ በእግዚአብሔር ፍጥረት ተደነቀ ። ይህንን ግዙፍ ዓለም በፈጠረ በእግዚአብሔር ዘንድ የሰው ልጅ የታሰበ ሆኖ እንዲገኝ ያደረገው ነገር ምን እንደሆነ ዳዊትን አልገባውም ነበር ። ጨረቃንና ከዋክብትን በፈጠረ በእግዚአ ብሔር ዘንድ የሰው ልጅ ሁሉ የታሰበ ሆኖ የመገኘቱ እርግጠኛነት ዳዊትን ደስ አሰኘው ።

በሌላም ጊዜ ነቢዩ ዳዊት ስለ ታላቅ እረኛነቱ ጽፎአል ። ይህም የታላቅ እረኛ ነቱ ዘመን የተባረከ ሕይወትን እንዳስገኘለት ተናግሮአል ።

«እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ፤ የሚያሳጣኝም የለም ። በለመለመ መስክ ያሳድረ ኛል ፤ በእረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል ። ነፍሴን መለሳት ፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድም መራኝ» በማለት ዘምሮአል ።

በዚሁ መዝሙሩ ላይ ስለ ተባረከው ሞት ተናግሮአል ፦— በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽ ናኑኛል ።

ስለ ተባረከው የዘለዓለም ሕይወቱ ተስፋ በመናገር ይህንን መዝሙሩን ይፈጽማል ፦— ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል በእግዚአብሔርም ቤት ለዘለዓለም እኖራለሁ ።

ዳዊት ቅን የሆነ ልብ ነበረው ። የተባረከ ሕይወትንም ተለማምዶአል ። የተባ ረከ አሟሟትም እንደሚኖረው ያውቅ ነበር ። ከሞተም በኋላ የተባረከ ሕይወት እንደሚኖረው የወደፊቱን አተኩሮ ተመልክቶአል ። አንተ እንዲህ ያለ ተስፋ አለህን ? ዳዊት ለኃጢአቱ ይቅርታ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ፈቃደኛ እንደሆነ አንተም ይኸንኑ ልታደርግ ትችላለህ ። ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ሲል አለቀሰ ፤ «ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ ከኃጢአቴም አንጻኝ ።»

ዳዊት ብዙ ጊዜ በመዝሙሩ አሰቃቂ ሞት ስለሚሞተው ሰው ይናገራል ። ስለሚያሾፉበትና ስለሚያላግጡበት እንዲሁም ግፍን ስለሚፈጽሙበት ሰው ይናገር ነበር ። ዳዊት ይህ ነገር ስለሚጠቅሰው ሰው እንዲህ ሲል ይናገራል ።

«የተመለከቱኝም ሁሉ በማላገጥ ሳቁብኝ ።»
«አጥንቶቼ ሁሉ ተለያዩ ።»
«ያለ ምክንያት የጠሉኝ ሁሉ ከራሴ ጠጉር በዙ ።»
«የሞት ኀዘንም ከበበኝ ።»
«የሲኦልም ሕመም ያዘኝ ።»
«መከራና ኀዘንም አገኘኝ ።»
«አጥንቶቼም ተቆጠሩ ።»
«ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፈሉ፤በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ ።»
«እኔ ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም በሰዎች ዘንድ እንደወንጀለኛና እንደተናቀ ሰው ተቆጠርኩ ።»
«ውሾችም ከበውኛል ።»
«እግሮቼንና እጆቼን ቸነከሩኝ ።»
«እኔም በሸክም ደከምኩ ።»
«በጥማቴም ጊዜ እንድጠጣው ሆምጣጤን ሰጡኝ ።»

ዳዊት ይህንን ነገር ይናገር የነበረው ስለ ማን ኖርዋል ? ስለ እራሱ አልነበረም የሚናገረው ፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው አድራጎት አልተፈጸመበትምና ነው ።

ዳዊት ይህንን የሚናገረው ስለ አንተ ኃጢአት ሊሞት ስለአለው ሰው ነው ። ጥናትህን ቀጥል ኃጢአትህን ይቅር ለማለት ስለ አንተ ስለሞተው በይበልጥ ትማራለህ ።

# ፯ኛ መልመጃ

## <u>ነቢዩ ዳዊት ።</u>

### እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ሰው

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ ። ትክክሉ ከሦስቱ አንዱ ነው ።

1. ዳዊት ያባቱን ——
   ሀ. በጎች ያግድ ነበር
   ለ. ላሞች ያግድ ነበር
   ሐ. ፈረሶች ያግድ ነበር ______________

2. ዳዊት ይዘምር የነበረው ——
   ሀ. በበገና ነው
   ለ. በመለከት ነው
   ሐ. በዋሽንት ነው ______________

3. ዳዊት የተናገረው —
ሀ. በደስታ ስለተሞላው ሰው ነው
ለ. መሳቂያ ማላገጫ ስለሆነው ሰው ነው
ሐ. ውኃ እንዲጠጣ ስለተሰጠው ሰው ነው ____________

4. ዳዊትን ስለ እግዚአብሔር ያልገባው —
ሀ. ሰው በእርሱ ዘንድ የታሰበ እንዲሆን መደረጉ
ለ. ሰማይን መፍጠሩ
ሐ. ምድርን መፍጠሩ ____________

5. ዳዊት ይናገር የነበረው —
ሀ. ስለተባረከው ሕይወትና አስከፊ ስለሆነው ዘለዓለማዊ ሕይወት ነበር
ለ. ስለተባረከው ሕይወናት አስከፊው ሞት ነበር
ሐ. ስለተባረከው ሕይወት ፣ ሞትና ዘለዓለማዊ ኑሮ ነበር ____________

ከትምህርቱ ከምታገኛቸው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. ዳዊት በምን ሸለቆ ውስጥ ነው ብልፍ ያለው ? ____________
7. ዳዊት ማንን ነው እረኛዬ ነው ያለው ? ____________
8. ዳዊት በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ይከተለኛል ያለው ምንድር ነው ? ____________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. ዳዊት መዝሙሮችን ጽፎአል ። ____________
10. ዳዊት እጅና እግሩ ስለ ተቸነከረው ሰው ተናግሮአል ። ____________

# ትምህርት ፳

## ኢየሱስ ክርስቶስ ።

ባለፉት ሰባት ትምህርቶች ብዙ ጠቃሚና እውነት የሆኑ ነገሮችን ተምረናል ። እስቲ ወደ ኋላ መለስ ብለን ጥቂቶቹን ትምህርቶች እንከልስ ።

**ትምህርት አንድ ፦ አንድ አምላክ**

በዚሁ ትምህርት ዓለምን የፈጠረውን የአንዱን እውነተኛ አምላክ መኖር ከማስ ተዋላችን በላይ በተጨማሪም ጥቂቶቹን የእግዚአብሔርን ባሕሪዎች ተምረናል ። እርሱም ይቅር ባይ አምላክ በመሆኑ በምህረቱ ሊራራልን ይችላል ።

**ትምህርት ሁለት ፦ አዳምና ሔዋን**

በሁለተኛው ትምህርታችን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ስለ አደረጉትና ስለ አልታዘዙት ስለ አዳምና ሔዋን ታሪክ አንብበናል ። መሐሪው አምላክም እንዴት መሸፈኛ እንዳዘጋጀላቸውም አስተውለናል ። አዳምና ሔዋን መሸፈኛ እንዲያገኙ ተንኰል የሌለበት እንስሳ ታረደ ።

## ትምህርት ሦስት ፡— ቃየንና አቤል

በዚህ ትምህርት የተማርነው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን እንድናገኝ ትክክለኛውን ዓይነት መስዋዕት ማቅረብ እንዳለብን ነው ። የቃየን መስዋዕት «የራሱን ሥራ የሚያመለክት» ስለሆነና እንዲህም ያለው መስዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስለሌለው መስዋዕታችን የቃየንን መስዋዕት በይመስል መልካም ነው ። «ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና» መስዋዕታችን የአቤልን የመሰለ የደም መስዋዕት መሆን አለበት ።

## ትምህርት አራት ፡— ነቢዩ ኖኅ

ኖኅ ከእግዚአብሔር ቁጣ የተከለለው በመርከብ ውስጥ ሆኖ እንደነበረ ሁሉ እኛም በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣው ከእግዚአብሔር ፍርድ ለመዳን ከለላ ያስፈልገናል ።

## ትምህርት አምስት ፡— ነቢዩ አብርሃም

በጉ ለአብርሃም ልጅ ምትክ ሆኖ እንደቀረበ አይተናል ፤ እንደዚሁም በኛ ምትክ ተተክቶ ሊሞት የሚገባው መስዋዕት ሊኖረን ይገባል ።

## ትምህርት ስድስት ፡— ነቢዩ ሙሴ

በዚህ ትምህርት በርያዎቹ አሰቃቂ ከሆነው ከእግዚአብሔር የሞት መቅሰፍት የበግ ደም የበራቸውን መዝጊያ ቀብተው እንደዳኑ ተምረናል ። እኛም ከእግዚአብ ሔር ቁጣ እንድናመልጥ የደም ቅብ ሊኖረን ይገባል ።

## ትምህርት ሰባት ፡— ነቢዩ ዳዊት

ዳዊት የተናገረው ስለ ሠራው ኃጢአቱ ምትክ ሆኖ መከራ ስለሚቀበልለት ሰው ነበር ። እግዚአብሔር እንዲቀበለን ብንፈልግ የሚፈለግብንን ነገር ሁሉ አሟልቶ ሊገኝ የሚችለውን ማግኘት ይኖርብናል ።

ይህም ሰው ለአዳምና ለሔዋን መሸፈኛ ሊሆን እንደተሰጠው እንስሳ መሸፈኛ ሊሆን ይገባል ። ይህም ሰው አቤል ለእግዚአብሔር እንዳቀረበው መስዋዕት መሆን አለበት ። ይህም ሰው መርከቡ ለኖኅና ለቤተሰቦቹ የከለላ ሥፍራ እንደሆናቸው ከለላ ሊሆን ይገባዋል ። ይህም ሰው አውራው በግ ለአብርሃም ልጅ ምትክ እንደ ሆነው ምትክ ሊሆን ይገባዋል ። በሙሴ ዘመን የነበሩት በሮች እንዳደረጉት ሁሉ ይህም ሰው ከሞት ፍርድ እንድንድን የደም ቅብ ሆኖን መቅረብ አለበት ። ይህም ሰው ተሹፎበትና ተላግጦበት እጅና እግሩ ተቸንክሮ የዳዊትን ትንቢት ሁሉ አሟልቶ የሚገኝ መሆን ይኖርበታል ።

ማን ይህን ሰው መሆን ይችላል ? ለነዚህ ነገሮች ሁሉ ብቁ መልስ ሆኖ ከመቅረቡም በላይ በሙላት የሚፈለግበትን አሟልቶ መገኘት የሚቻለውን ሰው ታውቃለህን ?

የነዚህን ማለት የያንዳንዳቸውን አላማዊ ምስጢር በሙላት አሳክቶ መፈጸም የሚቻለው አንድ ሰው ብቻ አለ ። ይህም ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ከዚህ አቋም ደረጃ እራሱን ማስተካከል የሚቻለው ማንም ሌላ ሰው የለም ። እግዚአብሔ

ርም ስለዚሁ ሲናገር «መዳንም በሌላ በማንም የለም ፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለም» ብሎአል ።

መቸ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህን ሁሉ ትንቢት ፍጻሜ ያሟላው ? ምን ጊዜ ኖርዋል መሸፈኛ የሆነው ? ምን ጊዜ ኖርዋል ምትክ የሆነው ? ምን ጊዜ ነበር ደሙን የቀባው ? በሕይወቱ በነበረበት ዘመን ነውን ? አይደለም በሕይወቱ በነበረ በት ዘመን ምንም ዓይነት ደም አልቀባም ነበር ። ታዲያ ምን ጊዜ ኖርዋል ይህንን ሁሉ ነገር ያደረገው ? ይህንን ያደረገበትን ጊዜ የሚያስረዳ አንድ መልስ ብቻ አለ ፤ ይኸውም በሞተ ጊዜ ነው ። በሞተ ጊዜ መሸፈኛ ሆነ ። በሞተ ጊዜ መስዋዕት ሆነ ። በሞተ ጊዜ መርከብ ሆነ ። በሞተ ጊዜ ምትክ ሆነ ። በሞተ ጊዜ ደሙን ቀባ ። በሞተ ጊዜ አዳም ፣ አቤል ፣ ኖኅ ፣ አብርሃም ፣ ሙሴና ዳዊት የተናገሩትን በሞላ ፈጽሞ ተገኘ ።

«ጌታ ኢየሱስ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም መስዋዕት ሆነ ። የልጁም የኢየ ሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል ።»

የእርሱ ሞት ድል መሆን አልነበረም ። የእርሱ ሞት ድል መንሳት ነበረ ። የእርሱ ሞት ማሸነፍ ነው ። እንዴት ነው አሸናፊነቱ ? ሞቱ ድል መንሳቱ ነበር ። ምክ ንያቱም በዚህን ጊዜ ነው አንተ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ምቹ መንገድ የምታገኘው ። በየሱስ ክርስቶስ ሞት በቀር ከዚህ በተለየ ሌላ መንገድ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ፈጽሞ አትችልም ። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ እንደሞተ አምነህ እንድትቀበለው ይለምንሃል ። አሻፈ ረኝ ብትል ግን ከእግዚአብሔር ተለይተህ ለዘላለም ትወድማለህ፣ትጠፋለህም ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የመጨረሻው አይደለም ። እግዚአብሔር ከመቃብር አስነስቶታል ። ይህም በሕይወቱ ከተፈጸሙት ማለት ደስ ከሚያሰኙት ታሪኮቹ አንዱ ነው ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቃብር ተነስቶአል ! ተነስቶም ከእግዚአብሔር ጋር ለመ ሆን ወደ መንግሥተ ሰማይ ሄዶአል ።

አሁን አንተ ማድረግ የሚገባህ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትክህ መቀበል ብቻ ነው ። እግዚአብሔርንም እንዲህ ማለት ይኖርብሃል ፣ «እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ፣ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ ስለዚህ እንድትቀበለኝ እፈልጋለሁ ። እኔ ተቀባይነትን የማገኝ በት መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንደምትኬ በመቀበል እንደሆነ አውቃለሁ ። በእኔ ምትክ እንደሞተ ተገንዝቤአለሁ ። የኃጢአቴንም እዳ እንደከፈለልኝ አምና ለሁ ።»

ይህንን ብትልና በእውነትም ማለትህ ከሆነ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ይቀበል ሃል ። ይህን በደረክ ጊዜ በንጹሕና በታመነ ሕይወት መኖር ትፈልጋለህ ። እግዚአ ብሔርም ይህን የመሰለውን ኑሮ እንድትኖር ይረዳሃል ። ኢየሱስ ክርስቶስን ግን በት ቀበል ለዘለዓለም ትጠፋለህ ።

ስለነዚህ ሁሉ በበለጠ ማወቅ ትፈልጋለህን ? ጥናትህን ቀጥል ።

# ፳ኛ መልመጃ

## ኢየሱስ ክርስቶስ ።

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ ። ትክክለኛው ከሦስቱ አንዱ ነው ።

1. እኔ ——
   ሀ. ጻድቅ ሰው ነኝ
   ለ. እንዳለሁ እንደኔነቴ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አገኛለሁ
   ሐ. ኃጢአተኛ ነኝ ______________
2. ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ——
   ሀ. እንደ ነፍሰ ገዳይ ሆኖ ነው
   ለ. በእኔ ምትክ ነው
   ሐ. እራሳቸውን መስዋዕት አድርገው ለሚያቀርቡ ምሳሌ ለመሆን ብቻ ነው___
3. ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ——
   ሀ. ድል መሆኑ ነበር
   ለ. ድል መንሳቱ ነበር
   ሐ. ኃጢአትን ለማስወገድ ያደረገው ሙከራ አሳዛኝ ነበር ______________
4. ከኃጢአቴ ሁሉ መንጻት የምችለው ——
   ሀ. በመልካም ሥራዬ ነው
   ለ. በሃይማኖቴ ነው
   ሐ. በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው ______________
5. ኢየሱስ ክርስቶስን ባልቀበል ——
   ሀ. ደህና ኑሮ ለመኖርና በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት እችላለሁ
   ለ. ከሞት በኋላ ሌላ ዕድል ያጋጥመኛል
   ሐ. ለዘለዓለም እጠፋለሁ ______________

ከትምህርቱ በምታገኘው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. አዳምና ሔዋን መሸፈኛ እንደነበራቸው ሁሉ የኛ መሸፈኛ ማን ነው ? ________
7. አቤል ተቀባይነት ያለው መስዋዕት እንደነበረው ሁሉ ተቀባይነት ያለው የኛ መስዋዕት ማን ነው ? ______________
8. የዳዊትን ትንቢት በሞላ የፈጸመው ማን ነው ? ______________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቃብር ተነስቶአል ። ______________
10. እግዚአብሔር እንዲቀበለኝ ብፈልግ ኢየሱስ ክርስቶስን ምትኬ አድርጌ መቀበል ይኖርብኛል ። ______________

# ትምህርት ፱

## ኃጢአት ።

ኃጢአት አደገኛው ጠላትህ ነው ። በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ከማግ ኘት ያግድሃል ። ከመንግሥተ ሰማያት ውጭ ያደርግሃል ፤ ወደ ሲኦል ይሰድሃል ። ኃጢአቶችህ ይቅር ካልተባሉ እውነተኛ ከሆነው አምላክ ዘንድ ለዘለዓለም የተወገ ድህ ትሆናለህ ።

«ያለ እግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን ይቅር የሚል ማን ነው ? ኢየሱስ ክርስ ቶስ በተባለው ሰው በኩል የኃጢአት ይቅርታ ስብከት እንደተሰበከልህ በአንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን ።»

ኃጢአት ምንድር ነው ?

ኃጢአት ስሕተት ብቻ አይደለም ። ኃጢአት መጥፎ ጠባይ ወይም ሱስ ብቻ አይደለም ። ኃጢአት የእግዚአብሔርን የክብር አቋም በለመታዘዝ ማጉደልም ነው ። በምናደርገውና በምንለው ሁሉ ከእግዚአብሔር ትክክለኛ አቋም ጋር እራሳ ችንን ባናስተካከል ኃጢአትን ማድረጋችን ነው ። ሰዎች ሁሉ በዚህ ነገር ወንጀለ ኞች ናቸው ። እግዚአብሔር «ኃጢአተኛነት ሕገወጥነት ነው» ይላል ።

የእግዚአብሔርን ሕግ ባፈረስን ጊዜ ኃጢአት እንሠራለን ። እግዚአብሔርንም በተቃቋምን ጊዜ ኃጢአትን ማድረጋችን ነው ። መጥፎ ነገሮችን ባሰብን ጊዜና በተና ገርን ጊዜ እንዲሁም እግዚአብሔርን የማያስደስት ነገር በፈጸምን ጊዜ ኃጢአትን ማድረጋችን ነው ።

ስንት ሰው ነው ኃጢአትን የሠራው ?

ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ሲል ቃተተ «እነሆ ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ ፥ እናቴም በኃጢ አት ወለደችኝ ።» ነቢዩ ዳዊት ኃጢአተኛ ነበር ።

እግዚአብሔርም አለ ፥ «ሁሉ በድሎአል ።» ፈጽሞ ኃጢአትን ያላደረገ አንድ ሰው ብቻ አለ ። ይኸውም ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ይህም የተጻፈው እርሱን በመጥቀስ ነው ፤ «ኃጢአትን አልሠራም ፥ በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም ። እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን ኃጢአት ያላወቀውን ስለኛ ኃጢ አት አደረገው ።»

«በእርሱ ኃጢአት ሳይኖርበት የኛን ኃጢአት ማስወገዱን ታውቃለህ ?» ከጌታ ኢየሱስ በስተቀር ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው ። ከአዳም ጊዜ ጀምሮ አሁን በዚህን ጊዜ የተወለዱ ሕፃናቶች እንኳ ሳይቀሩ ሰብዓዊ ፍጡር በሞላ የእግዚአብሔ ርን ክብር አጉድለዋል ።

የኃጢአት ዋጋ ምንድር ነው ?

«የኃጢአት ዋጋ ሞት ነው ።» አዳም ኃጢአት እንደሠራ ወዲያውኑ በመንፈስ ሞተ ። ከእግዚአብሔርም ተለየ ። ለሥጋዊም ሞት ተገዢ ሆነ ። በሥጋ ወዲያውኑ አልሞተም ነበር ፥ ነገር ግን ለሞት ተወሰነ ፤ ይህም ነገር በእርግጥ በእኛም ላይ የሚ

ፈጸም ነው። ምክንያቱም እኛ ኃጢአተኞችና ከእግዚአብሔር የተለየን በመሆናችን ነው። ከዚህም በቀር ኃጢአተኞች ስለሆንና የኃጢአታችንንም ዋጋ መቀበል ስለሚኖርብን ነው። የምንቀበለውም ዋጋ ሞት ነው። ይህም ማለት ስለ ኃጢአታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተወግደን በእሳት ባሕር ውስጥ እንሰቃያለን ማለት ነው። ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም እንዳንሰቃይ ማምለጫውን መንገድ መፈለግ ይኖርብናል።

ከኃጢአቴ እንዴት ነፃ መሆን እችላለሁ ?

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኜና ጌታዬ እንዲሆን በመጠየቅ ከኃጢአቴ ነፃ መሆን እችላለሁ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸክሞአል።

እስቲ ይህን ነገር ሳናልፈው እናስብበት

1. ሁላችንም በድለናል። «ኃጢአትን ባለማድረግ የጽድቅን ሥራ በመሥራት በምድር የሚኖር ከቶ አይገኝም።»
2. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤ ስለሆነም ኃጢአትን መመልከት አይቻለውም። «እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ በደልን የማይታገሱና ኃጢአትንም ማየት የማይችሉ ቅዱስ ዓይኖች አሉህ።»
3. ኃጢአቶቻችን ይቅር ከልተባሉልን ከእግዚአብሔር ተለይተን ለዘለዓለም እንወገዳለን «እናንተ አመፀኞች ከእኔ ተለዩ።»
4. ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን ይቅር ሊል ሞተ፣ «ክርስቶስ ያለ አምላክ ለሚኖሩ በደለኞች ሞተ።»
5. እግዚአብሔርም ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን ብንቀበለው ይቅር እንደሚለን ተናግሮአል። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።»

እግዚአብሔርም በእርሱ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት አንድ መንገድ ብቻ እንዳለ ተናግሯል። ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው። ኃጢአትህ ይቅር እንዲባልልህ ትፈልጋለህ ? እግዚአብሔር ይቅር እንዲልህ ጠይቀው፤ ወዲያውም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደምታምን ንገረው፤ አሁኑኑ ይህንን አድርግ።

# ፱ኛ መልመጃ

## ኃጢአት።

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ። ትክክለኛው ከሦስቱ አንዱ ነው።

1. ጠንቀኛው ጠላትህ ——
   - ሀ. ሕመም ነው
   - ለ. ኃጢአት ነው
   - ሐ. ኀዘን ነው ______________

2. ኃጢአት ማለት ——
   ሀ· መሳሳት ነው·
   ለ· መጥፎ ሱስ ወይም ልማድ ነው·
   ሐ· የእግዚአብሔርን የክብር ደረጃ ማጉደል ነው· ________

3. የኃጢአት ዋጋ ——
   ሀ· ሥጋዊ ሞት ነው·
   ለ· ጊዜያዊ የሆነ የሲኦል ውስጥ ስቃይ ነው·
   ሐ· በእሳት ባሕር ውስጥ ከእግዚአብሔር ፊት ተወግዶ መለየት ነው· ________

4. አንድ ሰው ብቻ ኃጢአትን አልሠራም ነበር እርሱም ——
   ሀ· አዳም ነው·
   ለ· አብርሃም ነው·
   ሐ· ኢየሱስ ክርስቶስ ነው· ________

5. ነቢዩ ዳዊት ——
   ሀ· ፍጹም የሆነ ሰው ነበር
   ለ· ኃጢአተኛ ሰው ነበር
   ሐ· መልአክ የሆነ ሰው ነበር ________

ከትምህርቱ በምታገኛቸው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ።

6. ኃጢአትን ይቅር ለማለት የሞተው ማን ነው ? ________
7. ቅዱስ የሆነና ኃጢአትን መመልከት የማይችለው ማን ነው ? ________
8. በእግዚአብሔር ዘንድ እንዴት ተቀባይነትን አገኛለሁ ? ________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ።

9. እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችን አድርገን ብንቀበል ይቅር እንደሚለን ነግሮናል። ________
10. ሁሉ በድሎአል። ________

# ትምህርት ፲

## ጸሎትና መልከም ሥራ።

ጸሎት ፦

ጸሎት በሰዎች ዘንድ ከታወቁት ኃይሎች አንዱ ነው። የማይወገዱ የሚመስሉትን መሰናከሎች በጸሎት ኃይል ማስወገድ እንችላለን። ከቶ በሥጋ ኃይል ሊታለፉ የማይቻሉትን ከባድና አስቸጋሪ የሆኑትን ድንበሮች በጸሎት ኃይል እናልፋቸዋለን። ሆኖም አራሳችንን ከእንደዚህ ካለው የጸሎት ዓይነት ጋር ከማለማመዳችን አስቀድሞ ለዚህ አድራጎት የሚፈለጉብንን ነገሮች አጠናቀን መገኘት ይኖርብናል።

1. ጸሎታችንን የምንጸልየው ወደ ትክክለኛው አምላክ መሆን አለበት ።

የድንጋይ አማልክቶች ጸሎትን መስማት አይችሉም ። የእንጨት አማልክቶችም ጸሎት ምን እንደሆነ አይገባቸውም ። ጸሎትን ሊሰማና ሊመልስ የሚቻለው እውነተኛውና ነዋሪ የሆነው አንዱ አምላክ ብቻ ነው ። ጸሎት መጸለይ የሚገባህ ለሰዎች ኃጢአት እንዲሞት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ምድር ወደ ላከው አምላክ መሆን ይገባል ።

2. ጸሎት ላይ ላዩን ያልሆነ ከልብ የሚደረግ ምለላ ሊሆን ይገባል ።

በጣም ሀብታም እንዲያደርግህ ወደ እግዚአብሔር ልትጸልይ አይገባም ፤ ምናልባት የአንተ ሀብታም መሆን የእርሱ ፈቃድ ላይሆን ይችላል ። የሚከተሉት ከሚሰማቸው የጸሎት ዓይነቶች ጥቂቶቹ ናቸው ።

ሀ. «እግዚአብሔር ሆይ ፣ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ ።»

ለ. «እግዚአብሔር ሆይ ፣ ለሕይወቴ ፈቃድህ ምን እንደሆነ እንዲገባኝ እርዳኝ ።»

ሐ. «እግዚአብሔር ሆይ ፣ ስለ አንተ ለሌሎች ምስክር እንድሆን በንጹህ ሕይወት እንድኖር እርዳኝ ።»

እግዚአብሔር ሌሎች ይሀን የመሳሰሉትን ጸሎቶች አድምጦ ይመልሳል ። ችግርህን ወደእርሱ እንድታቀርብ ይፈልጋል ። በሕይወትህ ባሉ በእያንዳንዱ ጥቃቅን ነገሮች ሊመራህ ይፈልጋል ።

3. ጸሎት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆን አለበት ።

«እንደፈቃዱ ብንጠይቅ ይሰማናል በማለት እንታመንበታለን ።» እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበሉትን ሰዎች ጸሎት አድምጦ ይመልሳል ። ጸሎታችንን ወዲያው አይመልስልን ይሆናል ። እንደ ፍላጎታችንም ላይመልስልን ይችል ይሆናል ። ይሁንና ለኛ መልካም የሆነውን ነገር ስለሚያውቅ ትክክል በሆነ መንገድ ይመልስልናል ።

4. ጸሎት በየሱስ ክርስቶስ ስም መሆን አለበት ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አማላጅ ነው ። ኢየሱስ ክርስቶስም አለ ፣ «ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትጠይቁ አባቴ ይሰጣችኋል ። ጸሎትህ እንዲመለስልህ ትፈልጋለህን ? ልትፈጽመው የሚገባህን ነገር አስታውስ ። ቁርጠኛ መሆንም ይኖርብሃል ። እንደፈቃዱም መጸለይ አለብህ ። በየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ ይኖርብሃል ።

*መልካም ሥራዎች ፡—*

መልካም ሥራ በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ ጠቃሚነት አለው ። ከሞላ ጎደል በሕይወቱ በዚህ ዓለም የኖረ ሰው ሁሉ ጥቂት መልካክም አድራጎቶችን ፈጽሞአል ። ጥቂቶች የታመሙ ሰዎችን እረድተዋል ። ጥቂቶቹም ለድሀ መጽውተዋል ። ጥቂቶቹም ለጠላቶቻቸው መልካም ብድራትን ፈጽመዋል ። እነዚህ ሁሉ መልካም ሥራዎች ናቸው ፤ የሆነ ሆኖ ከነዚህ ከበጎ ሥራዎች አንዱ ወይም በጠቅላ

ላው ሁሉም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት እንድትችል ሊያደርጉህ አይችሉም። እግዚአብሔርም መልካም ሥራችንና «ጽድቃችን ሁሉ እንደመርገም ጨርቅ ነው» ብሎአል። መልካም አድራጎት ነው ብለን የምንገምተው ሥራችን በእግዚአብሔር ፊት በእድፍ በክሉ እንደሚከረፋ ቁራጭ ጨርቅ ነው።

ምናልባት በጸሎት በመትጋት ቀንና ሌሊትም መልካከም ሥራዎችን ትሠራ ይሆናል። ነገር ግን በገሃነም ለዘላለም ትሰቃያለህ። በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን የምታገኝበት ጸሎትና መልካም ሥራ አይደለም። በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን የምታገኝበት አንዱና ትክክለኛው መንገድ በየሱስ ክርስቶስ ማመን ሲቻልህ ብቻ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስን አንዴ ከተቀበልክ በኋላ የምታደርገው መልካም ሥራ ሁሉ ጠቃሚ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወትህ ገዢ እንዲሆን በጠየከው ጊዜ ለሱ ለመኖር በመፈለግህ ታስደስተዋለህ።

«ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለምና» እግዚአብሔር ደኅንነታችንን በሥራችን ማግኘት እንዳንችል ያደረገበት ምክንያት በሥራችን ተመክተን እንዳንከራና እንዳንመጻደቅ ነው። እግዚአብሔር መመጻደቅን አይወድም፤ ዛሬም ሊቀበለው ለተዘጋጀ ሁሉ ስጦታውን በነፃ እየለገሠ ነው። በጸሎትህና በሥራህ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመቀበልህ ብቻ ይቅርታን ታገኛለህ። «ጸጋው በእምነት አድኖ አችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለምና።»

# ፫ኛ መልመጃ

## <u>ጸሎትና መልካም ሥራ።</u>

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ። ትክክለኛው ከሦስቱ አንዱ ነው።

1. ጸሎታችንን መጸለይ የሚገባን ——
   ሀ. ወደ ማንኛውም አማልክት ነው
   ለ. ወደ ማንኛውም ሰው ነው
   ሐ. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደላከው እግዚአብሔር ነው ____________
2. እግዚአብሔር የሚከተለውን ጸሎት ይመልሳል ——
   ሀ. እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ እኔ ኃጢአተኛውን ማረኝ
   ለ. እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ በለጸጋ አድርገኝ
   ሐ. እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ ታላቅ መሪ እንድሆን እርዳኝ ____________
3. እግዚአብሔር መልካም ሥራዎቻችን እንደሆኑ ተናገረ ——
   ሀ. ደስ የሚያሰኙት እንደሆኑ
   ለ. እንደ መርገም ጨርቅ እንደሆኑ
   ሐ. ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚወስዱን ____________

4. የኃጢአት ይቅርታ ——
ሀ. መልካም ሥራን በመሥራት ይገኛል
ለ. ገንዘብ በመክፈል ማግኘት ይቻላል
ሐ. የነፃ ስጦታ ነው ________

5. ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወትህ ገዢ በሚሆንበት ጊዜ——
ሀ. ለእርሱ በመኖርህ ታስደስተዋለህ
ለ. ዓለም በምትሰጠው ደስታ መደሰትን ትፈልጋለህ
ሐ. እጅግ ብዙ ገንዘብን ትፈልጋለህ ________

ከትምህርቱ በምታገኛቸው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. እግዚአብሔር ዛሬ የሚለግሰው ምንድር ነው ? ________
7. በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን የሚያስገኝ አንዱና እውነተኛው መንገድ ምንድር ነው ? ________
8. አንዴ ኢየሱስ ክርስቶስን ከተቀበልኩ በኋላ ምን ማድረግ ያስፈልገኛል ? ____

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. ጸሎት በሰዎች ዘንድ ከታወቁት ኃይሎች ውስጥ አንዱ ነው ። ________
10. ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ በሰውና በእግዚአብሔር መኃል ሆኖ ሊያማልድ ይችላል ። ________

# ትምህርት ፲፩

## ወደ ፊት ሊሆኑ ያላቸው ነገሮች ።

በጠቅላላው ማንኛውም ሰው ወደፊት ሊሆን ያለውን ነገር የማወቅ ጉጉት አለው ። ብዙ ሰዎች ወደፊት ሊሆን ያለውን ነገር ለመግለጽ ይጥራሉ ፤ ይሁንና ይህ ነገር በመብራራት እውቅ ሆኖ የተገለጸው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው ። የሆነ ሆኖ ወደፊት ሊሆን ካለው ነገር ጥቂቱን ገልጾልናል ።

**የክርስቶስ መምጣት ፡—**

ወደፊት ይሆናሉ ብሎ እግዚአብሔር ከነገረን ነገሮች አንዱ የኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝቦቹ ተመልሶ የመምጣቱ ጉዳይ ነው ። በእርሱ የታመኑት ሁሉ ከእነርሱ መኃል በመገኘቱ ደስታ ለዘለዓለም ደስ ይላቸዋል ። በእርሱ ያላመኑት ግን ከእርሱ ፊት ተነጥለው ይበረራሉ ። ኢየሱስ ክርስቶስ መቼ ተመልሶ እንደሚመጣ አናውቅም ። ዛሬ እንኳን ቢመጣ ዝግጁ ነህ ? አንዴ ከተመለሰ በኋላ ለደኅንነት በእርሱ ለማመን እርምጃ ለመውሰድ ሊቃጡ የሚሞክሩ በጣም ዘግይተዋልና አይቻላቸውም ። ከመመለሱ በፊት ልታምንበት ይገባሃል ። ለምን አሁን አታምነውም ?

**ታላቁ ነጭ ዙፋን ፡—**

ሌላው ወደፊት ይደረጋል ተብሎ የሚታመንበት ነገር ደግሞ የታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ ነው ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ያልተቀበሉት

ሁሉ በታላቁ በነጭ ዙፋን ፍርድ ፊት ይቀርባሉ። በዚያም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመናቃቸው ወይም በለመቀበላቸው ምክንያት ይፈረድባቸዋል። ማንኛውም በታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ ፊት የቀረበ ሁሉ ወደ ገሃነመ እሳት ይጣላል። እዚያ ትገኛለህን? ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝህ አድርገህ በታምንበት በዚያ ሥፍራ እንደምትገኝ እርግጠኛ ሁን።

ገሃነም ፦

ገሃነም አሰቃቂ ሥፍራ ነው። ወደ ገሃነም የሚወርዱ ሰዎች በብቸኝነት፥ በጭንቀት፥ በመከራና በጥማት እንደሚሰቃዩ ተነግሮናል። ገሃነም፥ እሳትና ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ሥፍራ ነው። ወደ ገሃነም ከሚሄዱት ውስጥ ለማምለጥ የሚቻለው የለም። ለዘለዓለም ከዚያው ይኖራሉ። «የመብገናቸው ጢስ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይወጣል፥ ቀንና ሌሊትም እረፍት የላቸውም።»

«ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኞችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል በሕር ነው።»

ወደ ገሃነም ከመሄድ እንዴት ትድናለህ? ከሞትክ በኋላ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የመቀበል ዕድል ሊገኝምህ አይችልም። በነጩ የፍርድ ዙፋን ፊት በቆምክ ጊዜ ክርስቶስን ለመቀበል ብትሞክር ዘግይተሃል ትባላለህ። ትክክለኛው ቀን ዛሬ ነው። አሁኑኑ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እመን ከዚያ በኋላ አሰቃቂ ከሆነው ከገሃነም ስቃይ እንደምታመልጥ እርግጠኛ ትሆናለህ። «እነሆ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው።»

መንግሥተ ሰማይ ፦

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው የተቀበሉ ሁሉ ለዘለዓለም በመንግሥተ ሰማይ ይኖራሉ፤ መንግሥተ ሰማይ የእረፍት፥ የሰላምና የደስታ ሥፍራ ነው። በመንግሥተ ሰማያት ከእግዚአብሔር ጋር በተሟላ አንድነት ሕብረት ይኖረናል። ይህም ሥፍራ ቅድስና የሌለው የሥጋዊ ፍትዎት ምኞት የሚረከበት ሥፍራ ሳይሆን ንጽሕናና ቅድስና የሰፈነበት ሥፍራ ነው።

አሁን ምርጫህን መወሰን አለብህ። አሁኑኑ ምርጫ ማድረግ ይኖርብሃል። መንግሥተ ሰማያትን ወይም ገሃነምን ምረጥ።

መቼ እንደምትሞት አታውቅም። ከአንድ ደቂቃ በኋላ ብትሞት ወዴት ትሄዳለህ? ወደ መንግሥተ ሰማይ ነው ወይስ ገሃነም ትሄዳለህ? ከነዚህ ከሁለቱ ሥፍራዎች ወደ አንዱ መሄድ የምትችለው የኃጢአትህን ይቅርታ እግዚአብሔርን በመጠየቅህና በለመጠየቅህ ብቻ ነው።

ወደ ገሃነም አትሂድ! ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድህ እርግጠኛ ሁን። ሕይወትህን ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስጥ።

# ፲፩ኛ መልመጃ

## ወደፊት ሊሆኑ ያላቸው ነገሮች ።

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ ። ትክክለኛው ከሦስቱ አንዱ ነው ።

1. ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመለስላቸው ——
   ሀ. ለኃጢአተኞች ሁሉ ነው
   ለ. ለሚጸልዩና መልካም ሥራን ለሚያደርጉ ሁሉ ነው
   ሐ. ለሚያምኑበት ሁሉ ነው ______________

2. መንግሥተ ሰማይ ——
   ሀ. የሥቃይ ሥፍራ ነው
   ለ. ሰላም ደስታና ፍሥኀ ያለበት ሥፍራ ነው
   ሐ. የሥጋ ፍላጎት የሚረካበት ሥፍራ ነው ______________

3. በነጩ የፍርድ ዙፋን ፊት የሚቀርቡ ሁሉ ——
   ሀ. ወደ ገሃነም ይሄዳሉ
   ለ. ወደ መንግሥተ ሰማይ ይሄዳሉ
   ሐ. ወደ ምድር ይወርዳሉ ______________

4. የወደፊቱን በትክክል ማወቅ የሚቻለው ——
   ሀ. እግዚአብሔር ነው
   ለ. መልአክ ነው
   ሐ. ሰው ነው ______________

5. ገሃነም ——
   ሀ. የደስታና የፍሥኀ ሥፍራ ነው
   ለ. የሥቃይ የጭንቀት የእሳትና የድቅድቅ ጨለማ ሥፍራ ነው
   ሐ. የጊዜያዊ ቅጣት መቀበያ ሥፍራ ነው ______________

ከትምህርቱ በምታገኛቸው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. ወደ ገሃነም የሚሄዱት ሰዎች ለምን ያህል ጊዜ በዚያ ይቆያሉ ? ______________
7. ለዘለዓለም የምኖርበትን ሥፍራ መምረጥ የሚቻለኝ መቼ ነው ? ______________
8. ከገሃነም ለማምለጥ በማን ማመን ይኖርብኛል ? ______________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበሉ ሁሉ በነጩ የዙፋን ፍርድ ፊት ይቀርባሉ ።
   ______________
10. ለመዳን ፥ ከመሞታችን በፊት ክርስቶስን መቀበል ይገባናል ። ______________

# ትምህርት ፲፪

## አንድ መንገድ ።

እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ አምላክ ብቻ እንደመኖሩ ሁሉ ወደ እግዚአብሔርም ዘንድ የሚያደርስ አንድ መንገድ ብቻ አለ ። ያ መንገድ ምንድር ነው ?

ጸሎት ይሆን ? አይደለም ጸሎት አይደለም ። መልካም ሥራ ይሆን ? አይደለም መልካም ሥራ አይደለም ። ገንዘብ መክፈል ይሆን ? አይደለም ገንዘብ መክፈል አይደለም ። የተቻለህን ያህል የምታደርገው መልካም አድራጎት ይሆን ? አይደለም የተቻለህን ያህል የምታደርገው መልካም አድራጎት አይደለም ። ታዲያ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደው መንገድ ምንድር ነው ?

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ተናገረ ፣ «እኔ መንገድ ነኝ ።» እርሱ ብቻ ነው ትክክለኛው መንገድ ? አዎ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያደርሰው ትክክለኛው መንገድ እርሱ ብቻ ነው ። ከእንግዲህ ፍጽምና የሌለው ደካማ የሆነ የሰብዓዊ ፍጡር መሪ ትክክለኛውን የመንግሥተ ሰመያትን መንገድ ሊያመለክተን አይችልም ። ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ትክክለኛውን የመንግሥተ ሰማይ መንገድ አመልክቶናል ። ይኸውም እርሱ እራሱ ብቻ ትክክለኛው መንገድ እንደሆነ ነው ። ኢየሱስ ክርስቶስን ካልተከተልን ፈጽሞ መንግሥተ ሰማይ መሄድ አንችልም ።

እቅድ እንድታደርግ የሚገፋፋህ ነገር ይገጥምሃል ። በዚህም ምርጫህ የሞትን መንገድ ይዘህ ወደ ዘለዓለም ሞት ወደ ገሃነም ወይም የሕይወትን መንገድ ይዘህ ወደ መንግሥተ ሰማይ መሄድ ትችላለህ ።

እግዚአብሔር የዘለዓለም ሕይወትን መንገድ እንድትመርጥ እንደሚፈልግብህ ሁሉ ሰይጣንም በበኩሉ የዘለዓለም ሞትን መንገድ እንድትመርጥ ይፈልጋል ። እግዚአብሔር የመንግሥተ ሰማያትን መንገድ ይዘህ እንድትሄድ አያስገድድህም እንደዚሁም ሰይጣን የገሃነምን መንገድ ይዘህ እንድትሄድ አያስገድድህም ። አንተ የግል ምርጫህን የመወሰን መብት አለህ ። የዘለዓለም ኑሮህን ልታሳልፍ የምትወድበትን ሥፍራ አንተው እራስህ መምረጥ ትችላለህ ። ዛሬውኑ መምረጥ ይኖርብሃል ።

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የማታምን ከሆንክ ወደ ገሃነም ለመሄድ በመንገድህ ላይ ነህ ። ዛሬ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የማትመርጥ ከሆነ ወደ ገሃነም በሚያደርሰው መንገድህ ላይ ጉዞህን በመቀጠል ላይ ነህ ። እቅድ ለማድረግ ባትወስን የዘለዓለም ሞትን መምረጥህ ነው ። ነገ ምርጫህን ብታደርግ ምናልባት ይዘገይብህ ይሆናል ። ምናልባትም ትሞት ይሆናል ። «እነሆ የተወደደው ጊዜ አሁን ነው ፤ እነሆም የመዳን ቀን ዛሬ ነው ።»

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአትህ በመስቀል ላይ ሞቶአል ። በአንተ ሥፍራ ተተክቶ ሞቶአል ። ያንተን ቅጣት ወስዶአል ። «ስለ በደላችን ቆሰለ ፣ ስለ መተላለፋችንም ደቀቀ ። በመገረፉም ቁስል ተፈወስን ። ሁላችንም እረኛ እንደሌላቸው በጎች ጠፋን ፤ እያንዳንዱም ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ ። እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ ።»

ይህን ላንተ የሞተውን ኢየሱስን መቀበል ይኖርብሃል ። እግዚአብሔርንም እን ዲህ ልትለው ይገባሃል ፤ «እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፣ ወደ ገሃነምም መሄድ ይገባኛል ። ኢየ ሱስ ለኔ ኃጢአት እንደሞተ አምናለሁ ። አሁን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ተቀብዬ ዋለሁ ፤ ከእንግዲህም ወዲያ ባለው የሕይወት ዘመኔ ለእርሱ ለመኖር ቆርጫለሁ ።»

አንድ አምላክ፣ አንድ መንገድ፣ እርግጥ ነው አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ አለ ። የቀሩት አምላኮች አምላክነት ሐሰት ነው ። አንድ እውነተኛ የሆነ መንገድ ብቻ አለ ። የቀሩት መንገዶች እውነተኛ መንገድነት ሐሰት ነው ። ለምን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝህ ተቀብለህ በመንግሥተ ሰማይ መንገድ ላይ ለመሆንህ እርግ ጠኛ አትሆንም ? ኢየሱስ «ወደ እኔ የሚመጣውን ወደ ውጭ አላወጣውም» ብሎአል ።

# ፲፪ኛ መልመጃ

## አንድ መንገድ ።

በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መስመር ላይ የትክክለኛውን መልስ ፊደል ጻፍ ። ትክክለኛው ከሦስቱ አንዱ ነው ።

1. ኢየሱስ ክርስቶስ የቆሰለው ——
   ሀ. ስለ እኛ መተላለፍ ነው
   ለ. ስለ እራሱ መተላለፍ ነው
   ሐ. ስለ መላእክት ነው ____________

2. አንዱና አንድ ብቻ የሆነው ወደ እግዚአብሔርና ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚያ ደርሰው መንገድ ——
   ሀ. ጸሎት ነው
   ለ. መልካም ሥራ ነው
   ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ____________

3. ሰይጣን ምርጫ እንድታደርግ የሚፈቅደው ——
   ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝህ አድርገህ ለመቀበል እንድትመርጥ
   ለ. ወደ ዘለዓለም ሞት የሚያደርሰውን መንገድና ገሃነምን እንድትመርጥ
   ሐ. ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚያደርሰውን መንገድ እንድትመርጥ ____________

4. ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ——
   ሀ. የነቢያትን ትንቢት ሊፈጽም ብቻ ነው
   ለ. የኃጢአትህን ቅጣት በሞቱ ሊቀበል ነው
   ሐ. በነፍሰ ገዳይነቱ ሊሞት ነው ____________

5. ጌታን ለመቀበል የሚያመቸው ጊዜ ——
   ሀ. ሕይወትህን በምታድስበት ጊዜ ነው
   ለ. በምታረጅበት ጊዜ ነው
   ሐ. አሁን ቃሉን በምትሰማበት ጊዜ ነው ____________

ከትምህርቱ በምታገኛቸው ጥቂት ቃላቶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ።

6. የትኛውን መንገድ ነው እግዚአብሔር እንድንመርጠው የሚፈልግብን ? ____________________

7. ለምንድር ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንገላታት የደቀቀው ? ____________________

8. የዘለዓለምን ሞት እንድትመርጥ የሚፈልግብህ ማን ነው ? ____________________

አይደለም ወይም ነው በማለት መልስ ።

9. አንድ አምላክ ብቻ አለ ። ____________________

10. በኃጢአተኝነትህ ወደ ገሃነም መግባት ይገባሃል ። ____________________

ተወዳጁ ተማሪያችን ሆይ ፣

እነሆ አሁን ወደዚህ ትምህርታችን መጨረሻ መምጣትህ ነው ። በዚህ ላይ በማከል አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እወዳለሁ ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝህ አድርገህ ተቀብለኸዋልን ? እምናለሁ ! ይህ ልታደርገው የሚገባህ ታላቁና የመጀመሪያው እቅድ እንደሆነ ። በተጨማሪ ልጠይቅህ የምወደው ፦

1. በሕይወትህ ዘመን ወንጀለኛና የጠፋህ ኃጢአተኛ እንደሆንክ የተሰማህ ጊዜ አለ ?

መልስ ፦ ____________________

2. በሕይወትህ ዘመን ክርስቶስ ኃጢአትህን በመሸከም በአንተ ሥፍራ ተተክቶ እንደሞተልህ በልብህ ያመንክበት ጊዜ አለ ?

መልስ ፦ ____________________

3. በእምነት ተነሳስተህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በአክብሮት የሕይወትህ ታላቁ ጌታ እንዲሆን ቁርጥ ሐሳብ በማድረግ ለመቀበል እርምጃ የወሰድክበት ጊዜ በሕይወትህ ዘመን አለ ?

መልስ ፦ ____________________

የዘለዓለምን ሕይወት እንደምትወርስ እርግጠኛ ሳትሆን ጥቂት ችግርና ጥያቄ ኖሮህ የሚረዳህ ሰው ቢያሻህ በድራሻችን በኩል ጻፍልን ።

ሌላ ኮርስ ያሻሃል ? ሌላ ኮርስ የሚያሻህ ወይም የሚያስፈልግህ ቢሆን አድራሻህን ጽፈህ በድራሻችን በጽሑፍ ጠይቀን ።

ማናቸውም መንፈሳዊ ጥያቄዎች ቢኖሩህ ለቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ ድርጅት የፖ. ሣ. ቁ. 127 አዲስ አበባ ብለህ ብትጽፍልን ይደርሰናል ።